# ቁልፍ እይታወች፡ በሰሜን ኢትዮጵያ ለተፈጠረው ግጭት የማህበራዊ ሳይንስ የአደጋ ጊዜ ምላሽ ምልከታዎች

**SSHAP**
**Social Science in Humanitarian Action Platform**

ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በርካታ ተደራራቢ ሰብአዊ ቀውሶች፤ ግጭት፣ የአየር ንብረት መዛባት፣ኮቪድ-19፣ የበረሃ አንበጣ እና ሌሎችም ጨምሮ እያጋጠማት ነው። እነዚህ ተደራራቢ ቀውሶች ወደ 30 ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብን ለምግብ ዋስትና እጦት፣ መፈናቀል እና የጥበቃ ስጋቶች ዳርገዋል። [1,2] በሰሜን ኢትዮጵያ በሚገኙት በትግራይ፣ አማራና አፋር ክልሎች በህዳር ወር 2013 በተጀመረዉና ቀጣይነት ባለዉ ግጭትና ግጭቱን ተከትሎ በተከሰተዉ ሰብአዊ ቀውስ ምክንያት፣ በየካቲት ወር 2014 ከ2.5 ሚሊዮን በላይ የሚገመት ህዝብ የተፈናቀለ ሲሆን በግንቦት ወር 2014 ብቻ 9.4 ሚሊዮን የክልሉ ህዘብ ሰብዓዊ እርዳታ ያስፈልጋቸው ነበር ። [3] የግል እና የህዝብ ሀብት ወድሟል፣ ቀድሞውንም የነበረዉ ደካማ ኑሮ ተጎድቷል፣ ማህበረሰቦች ከፍተኛ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል።.

ይህ ፅሁፍ የሰሜን ኢትዮጵያ ቀውስ ጠቃሚ አውዳዊ ሁኔታዎችን እና ማህበራዊ ተፅእኖዎችን ይዘረዝራል። በተጨማሪም የሰብአዊ ምላሽን ውጤታማነት ለማሻሻል ቁልፍ እይታወችን ያቀርባል። ፅሁፉም የተዘጋጀዉ ነባር የታተሙ እና ያልታተሙ ጽሑፎችን በፍጥነት በመገምገምና እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ፣ ከተጎዱ ክልሎች የመጡ ሰዎችን እና የሰብአዊ እርዳታ ሰጪዎችን ጨምሮ በተደረጉ ውይይቶች ነዉ። ይህ ጽሁፍ ፤ ማህበራዊ ሳይንስ በሰብአዊ ድርጊት መድረክ (Social Science in Humanitarian Action Platform Fellowship) ተሳታፊዎች መድረክ በሚዘጋጀው ተከታታይ ክፍል ላይ አንድ አካል ሲሆን ከምድብ 2 (cohort 2) በሄራን አበበ እና ጌታቸው በላይነህ የተጻፈ ነዉ። ይኽ ጽሁፍ በኢዛና አምደወርቅ (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) ፣ቀለመወርቅ ታፈረ (መቐለ ዩኒቨርሲቲ) እና ዮሚፍ ወርቁ (ገለልተኛ የሰብዓዊ ጉዳዮች አማካሪ) ተገምግሞ በልማት ጥናት ተቋም (Institute of Development Studies) ስር በሚገኘው ማህበራዊ ሳይንስ በሰብአዊ ድርጊት መድረክ (SSHAP) ቡድን አባል በሆነችው በጣቢታ ህሪኒክ ድጋፍ የተዘጋጀ ነዉ። ጽሁፉን በኃላፊነት ያዘጋጀዉ ደግሞ ማህበራዊ ሳይንስ በሰብአዊ ድርጊት መድረክ (SSHAP) ነው።

## ቁልፍ እይታወች

### የብሄረሰብ እና የፖለቲካ ውጥረቶች እና የአናሳ ብሄረሰብ ቡድኖችን ማካተት

- **ምላሽ ሰጪዎች ድጋፍ ሲያደርጉ ለተለዩ የፖለቲካ ወይም ታጣቂ ቡድኖች፣ በተለይም ከሰብአዊ መብት ረገጣ ጋር ለተገናኙ ቡድኖች (የመንግስት አካላትን ጨምሮ) ድጋፍ ከማድረግና የወገንተኝነት ስሜት ከማሳየት መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል።** የብሔር እና የፖለቲካ ውዝግቦች፣ የሰብአዊ እርዳታን አላግባብ ከመጠቀም አንፃር በተፈጠረ አለመተማመን እና በነበሩ ገደቦች ምክንያት ፤ የእርዳታ ስርጭትን እና እርዳታን ዉስብስብ ሊያደርጉ ስለሚችሉ በተቻለ መጠን በጥንቃቄ መቃኘት አለባቸው ።
- **ሁከት የሌላቸው የሲቪል ማህበረሰብ ቡድኖች ፤ ዳያስፖራ/ዓለም አቀፍ ኔትወርኮችን ጨምሮ፤ ምላሽ ሰጪዎች የበለጠ ትርጉም ባለው መልኩ ሊያሳትፉዋቸው የሚችሏቸው አስፈላጊ ተዋናዮች ሊሆኑ ይችላሉ ።** እንደዚህ ያሉ አውታረ መረቦች የሰብአዊ ምላሽ ክፍተቶችን ለመፍታት አስፈላጊ መንገዶች ሊሆኑ ይችላሉ ። የብሔር ግንኙነት ከፖለቲካ አሰላለፍ ወይም ከግጭቱ ውስጥ 'ወገን' ጋር መያያዝ ስለሌለበት ፤ ምላሽ ሰጪዎች ሊከሰቱ የሚችሉ ፖለቲካዊ ስሜቶችን ማወቅ አለባቸው።
- **ምላሽ ሰጪዎች ጉዳት በተከሰተባቸዉ ክልሎች ዉስጥ የተጎዱትን አናሳ ብሄረሰቦችን ለመድረስ ጥረታቸውን ማሳደግና በተጨማሪም በውስጥ ተፈናቅለዉ በሚገኙባቸው አካባቢዎች መደገፋቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።** እነዚህ ቡድኖች በሰብአዊ ምላሽ ችላ ተብለዋል። ለምሳሌ ትግራይ ውስጥ ይሄ በኤርትራ አዋሳኝ አካባቢዎች የሚገኙትን ኢሮቦችን እና ኩናማዎችን ያጠቃልላል። በተጨማሪም ብዙ አገው/ካሚርም በአማራ ክልል በተለይም በሰቆጣ ተፈናቅለዋል።
- **ምላሽ ሰጪዎች ከአካባቢው ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ቋንቋዎች፣ ልማዶችእና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች ለመለየት በየአካባቢው አውታረ መረቦች ውስጥ በመግባት እና ተርጓሚዎችን በማሳተፍ አካታች እገዛን**

**ማረጋገጥ አለባቸው።** የአናሳ ቡድኖች ዩቋንቋ ፣ ሃይማኖታዊ እና ሌሎች ባህላዊ ገጽታዎች የተለያዩ ሊሆኑ ስለሚችሉ ፤ ሁሉንም በአንድ አይነት አቀራረብ መቅረብ ስኬታማ ላያደርግ ይችላል።

## ተለዋዋጭነት ላለዉ መፈናቀል ምላሽ መስጠት

- **የምላሽ ተግባራት የተፈናቃዮችን እና የተቀባይ ማህበረሰቦችን ፍላጎት በተለያዩ ረገዶች የሚፈቱ መሆን ይገባቸዋል።** ይህም በኣካባቢዉ ባሉት ሀብቶች ፍላጎታቸዉ ያልተሟላ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ካምፖች እና ማህበረሰቦችን ፤ እንዲሁም እንዲሁም ከቦታ ቦታ በእንቅስቃሴ ላይ ያሉ ማህበረሰቦችን አርብቶ አደሮችን ጨምሮ ያጠቃልላል።
- **ምላሽ ሰጪዎች፤ የመጠለያ ቦታዎች እና እንደ መጸዳጃ ቤት እና ምግብ ስርጭት ያሉ የአገልግሎት መዳረሻ ቦታወች፤ የደህንነትና የመንቀሳቀስ ተግዳሮቶች ያሉባቸዉ ተፈናቃዮችን ግምት ውስጥ ያስገቡ መሆናቸዉን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።** መሠረተ ልማቱ በደረቅ እና እርጥብ ወቅታዊ ሁኔታዎች ቀጣይነት ያለዉና ደህንነቱ የተጠበቀ አገልግሎት መስጠቱን እንዲያረጋግጥ ሆኖ ሊጠናከር ይችላል። ዝናብ በተለይም ለልጆች፣ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች አዲስ ተግዳሮቶችን ከማምጣቱ በተጨማሪ የተላላፊ በሽታዎችን ስጋት ያመጣል። ደረቅ ወቅቶች ወደ ከፍተኛ የውሃ እጥረት ሊያመራ ይችላል፣ ሴቶች እና ልጃገረዶች ዉሃ ለመቅዳት ተጨማሪ ጉዞ እንዲያደርጉ ይጠይቃሉ።
- **እንደ ገቢ ማጣት፣ ትምህርት፣ ጤና፣ ጥበቃ፣ የምግብ ተደራሽነት እና ቀጣይነት ያለው የደህንነት ስጋቶች የመሳሰሉ የተመላሾች ስጋት ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ምላሾች ሆነዉ መቀጠል ይኖርባቸዋል።** ተመላሾች መተዳደሪያቸዉ ተጎድቶ (ለምሳሌ የግብርና ሰብሎች እና ግብአቶች መጥፋት) እና ያልተመለሱ ወይም አገልግሎት የማይሰጡ መሰረታዊ አገልግሎቶች ሊያጋጥማቸው ይችላል።.

## አውድ- ተገቢ የሆነ የጤና እና ደህንነት ምላሽ

- **በስፋት ከሚስተዋለው ወሲባዊና እና ጾታ-ተኮር ጥቃት (SGBV) አደጋ ለተረፉ ሰዎች ድጋፍ እንዲሰጡ የአካባቢ መሪዎችን፣ ተፅዕኖ ፈጣሪዎችን እና ተቋማትን ማሰልጠን** እንዲሁም **ድጋፍ ማድረግ ወሳኝ ነው።** ወሲባዊና እና ጾታ-ተኮር ጥቃት (SGBV) የተስፋፋ እና እንደ የጦር መሣሪያ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። ከወሲባዊና እና ጾታ-ተኮር ጥቃት (SGBV) አደጋ የተረፉ ብዙ ሰዎች መገለል ይሰማቸዋል፣ ይህም ፈቃደኛ ሆነዉና ፍላጎት ኖሯቸዉ ድጋፍ እንዳያገኙ ተጽዕኖ ያሳድርባቸዋል። የክርስቲያን እና የእስልምና ሀይማኖት መሪዎች በወሲባዊና እና ጾታ-ተኮር ጥቃት (SGBV) ያሉ ደንቦቹን እና አመለካከት ለመለወጥ እና ለማገዝ እንዲሁም ከጥቃት ለተረፉ ሰዎች የሚደረግን የሪፈራል እና የአገልግሎት አቅርቦትን መደገፍ ይችሉ ይሆናል። በተጎዱ ክልሎች ውስጥ ባሉ የቤተሰብ ጉዳዮች የሚወስኑ 'የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች' የአካባቢ ሰራተኞች - የመንደር ደረጃ ተቋማት (ብዙውን ጊዜ ወንድ በበላይነት የሚመራቸዉ) - በተመሳሳይ መልኩ ሊሠለጥኑ ይችላሉ። በክርስቲያን ማህበረሰቦች ውስጥ የተለመዱ ነጠላ-ጾታ የቡድን ኃይማኖታዊ ማኅበራት፣የጋራ ፈውስ እና የስነ-ልቦና እና የማህበራዊ ድጋፍን ለማስተላለፍ ምቹ ቦታዎች ሊሆኑ ይችላሉ።
- **በተፈናቃዮች መካከል ያሉ ተጋላጭ ቡድኖች፣እንደ ሴቶች፣ ልጃገረዶች፣ አረጋውያን ግለሰቦች እና አካል ጉዳተኞች የቁልፍ አገልግሎቶችን ቦታ በመንደፍ እና በመወሰን ላይ መሳተፍ አለባቸው።** የጤና አገልግሎቶች፣ የንፅህና መጠበቂያ ተቋማትን ጨምሮ፣ እንደ ግላዊነት እና ደህንነት በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ በቂ ያልሆነ ወይም ያልተመጣጠነ የሥርዓተ-ፆታ ዕይታ አላቸዉ። ለእነዚህ ተጋላጭ ቡድኖች የአገልግሎት ቦታ ርቀትም ቁልፍ ፈተና ነው።
- **ምላሹ ለነፍሰ ጡር ሴቶች የጤና አገልግሎት የሚሰጡትን አገልግሎት ሰጪዎች ጾታ**ን **ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።** ያለፉት ጥናቶች እንደሚጠቁሙት፣ በአፋር ማህበረሰብ የጤና ሰራተኞች ጾታ በእርጉዞች እና የሚያጠቡ እናቶች እንክብካቤን በመፈለግ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ጠቁመዋል።
- **ምላሽ ሰጪዎች የአዋቂዎች የጤና እንክብካቤ አስፈላጊነት እና አቅርቦት ላይ ትኩረት ማድረግ አለባቸው።** አዋቂዎችን ስለ ጤንነታቸው ለማሳተፍ አንዱ እድል ከልጆች ጤና አገልግሎቶች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ወቅት ሊሆን ይችላል። በክልሉ ውስጥ ያለፉ ጥናቶች በሁሉም ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደረጃዎች ውስጥ ያሉ ቤተሰቦች ለህፃናት ጤና ስጋቶች አስቀድመው እንክብካቤ እንደሚፈልጉ ጠቁመዋል:: ሆኖም፣ አዋቂዎች - በተለይ አቅማቸው ውስን የሆኑ - ለራሳቸው የጤና እንክብካቤ ላይፈልጉ ይችላሉ። ይህ በግጭቱ ውስጥ ተባብሶ ሊሆን ይችላል።.

- **ተገቢ፣ ዘላቂነት ያለው የአእምሮ ጤና ድጋፍ አስፈላጊ ነው።** እንደ ማህበር እና ሌሎች (ከዚህ በታች ይመልከቱ) የታመኑ የሃይማኖት እና ሌሎች የአካባቢ አውታረ መረቦችን እና ተቋማትን መጠቀም ተደራሽነትን ሊያሳድግ ይችላል። ከግጭቱ የሚመጡ የስነ ልቦና ጉዳቶችን ጨምሮ የአእምሮ ጤና ጉዳዮች ዋና አሳሳቢ ጉዳዮች ናቸው።
- **ከአገሬው ተወላጆች ወይም ከሀይማኖ**ታዊ **ፈዋሾች እና ልማዶች ጋር መሳተፍን አስቡ።** ባህላዊ ልማዶች (እፅዋትን፣ ፀበል እና ጸሎትን ሊያካትት ይችላል) በስፋት የሚከወኑ ሆነው ሊቀጥሉ እና በችግር ጊዜ ከዘመናዊ ህክምና የበለጠ ተደራሽ ሊሆኑ ይችላሉ።

### በግጭት የተጎዱ ልጆችን እና ወጣቶችን መደገፍ

- **ወጣቶች እና ህፃናት ለአጭር እና የረዥም ጊዜ ግጭት-ነክ ጉዳቶች በጣም የተጋለጡ ስለሆኑ፣ ምላሹ ለነዚህ ማህረሰብ ጥበቃ ጉዳዮች ቅድሚያ መስጠት አለበት።** የትምህርት ማጣት፣ የልጅነት ጋብቻ፣ አካላዊ ጥቃት፣ በትጥቅ ግጭት ውስጥ መግባት፣ ከቤተሰብ መለያየት፣ የአእምሮ ጤና ስጋቶች እና የምግብ ዋስትና ማጣትን ጨምሮ በርካታ አደጋዎች ያጋጥሟቸዋል። እነሱ፣ ወይም ቤተሰቦቻቸው፣ እንደ ብዝበዛ ስራ ያሉ አሉታዊ የመቋቋም ስልቶችንም ሊጠቀሙ ይችላሉ።

### ሰላምን መደገፍ እና በአካባቢ በዘላቂታዊ መቋቋም

- **ፖለቲካዊ እና በጎሳዎች መካከል ግጭት ሲፈጠር ሁሉን አቀፍ የአካባቢ ሰላም ግንባታ ጥረቶችን መደገፍ ወሳኝ ነው።** እነዚህ ጥረቶች የማህበረሰብ መሪዎችን እና ብዙም ተፅእኖ የሌላቸው የማህበረሰብ አባላትን (ወጣቶች፣ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች) መለየትና ማሳተፍ አለባቸው። በአፋር ህዝብ መካከል የመግባቢያ እና የአፈፃፀም ስርዓት የሆነው እንደ ዳጉ ያሉ የአካባቢ ባህላዊ ተቋማት መጠቀም የተለያዩ ቡድኖችን የማሳተፍ አንዱ መንገድ ሊሆን ይችላል።
- **አጣዳፊ ፍላጎቶችን ለመቅረፍ የሚከናወኑ ጥረቶችን ላይ ኢንቨስት ያድርጉ፣ ይደግፉ እና በግጭቱ ክፉኛ የተጎዱ የአካባቢ ተቋማትን መልሰዉ እንዲያገግሙ እና ዘላቂ የመቋቋም ችሎታ እንዲኖራቸዉ ይደግፉ።** ይህ ለአገልግሎት እና ለመሠረተ ልማት ቴክኒካል አቅም ብቻ ሳይሆን ህብረተሰቡን ያሳተፈ ተሳትፎ እና ለመደበኛ እና መደበኛ ያልሆነ ማህበረሰብ ተኮር ድርጅቶች ማጠናከሪያ ድጋፍን ማካተት አለበት። እቁብ እና እድር በአካባቢ ደረጃ የሚከናወንን ድጋፍ ፣ ሰብአዊ እርዳታ ፣ ማገገም እና መቋቋም ሊያሳልጡ የሚችሉ በሁሉም ግጭት በተከሰተባቸው ክልሎች የሚገኙ አካባቢያዊ ተቋማት ናቸዉ።

## የግጭቱ ሁኔታ

ኢትዮጵያ 120 ሚሊዮን ህዝብ እና ከ81 በላይ ብሄረሰቦች ያላት ሀገር ናት። የአስተዳደር ሥርዓቱ የተደራጀው 'በብሄር ፌዴራሊዝም' ዙሪያ ነው።.[4] ይህ ማለት እያንዳንዱ ራሱን የሚያስተዳድር፣ ጉልህ የሕግ አውጭ እና አስፈፃሚ ሥልጣን ያለው ክልል፣ ከተለየ የብሔረሰብና ቋንቋ ቡድን ጋር የተቆራኘ ነው። ይህ በቡድን እና በክልሎች [5]፣ እና በክልሎች እና በፌደራል ባለስልጣናት መካከል የቆየ አለመግባባት ፈጥሯል። በፌዴራል መንግስት እና በትግራይ ክልል አውራ የፖለቲካ ፓርቲ በህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) መካከል ያለው ውጥረትም ለአሁኑ ግጭት መንስኤ ነው።[6]

የሰሞኑ እና እየቀጠለ ያለው ብጥብጥ የተቀሰቀሰው በህዳር 2013 ህወሀት በትግራይ ክልል ዉስጥ ባሉት የፌደራል ወታደራዊ ካምፖች ባደረሰው ጥቃት እና የኢፌዲሪ መንግስት በሰጠው ወታደራዊ ምላሽ ነው።.[7,8] ይህ ምላሽ የተሰጠዉ የኢትዮጵያ ብሄራዊ መከላከያ ሰራዊት ከኤርትራ ወታደሮች እና አልፎ አልፎም ከክልል ታጣቂዎች ጋር በመተባበር ነው።[9,10] በአንዳንድ የግጭቱ ደረጃዎች በዜጎች እና በሲቪል ማህበረሰብ በተለይም በደቡብ የሀገሪቱ ክፍል በትጥቅ ለታገዘ የመንግስት ጣልቃገብነት ህዝባዊ ድጋፍ ታይቷል።

ሕወሃት በፌዴራል መሥሪያ ቤቶች ላይ የፈጸመው ጥቃት – የፌዴራል ጣልቃገብነትን ለማክሸፍ በአስፈላጊነቱ በሕወሃት የተገመተው[10] – ራሱ የሕወሃት ባለስልጣናት ሰፊ የእምቢተኝነት እንቅስቃሴ አካል ነበር። በመስከረም 2013፣ በኮቪድ-19 ምክንያት ሀገራዊ ምርጫ እንዲራዘም የፌደራል መንግስት ትእዛዝ ቢሰጥም እነዚህ ባለስልጣናት የክልል ህግ አውጪ ምርጫዎችን አካሂደዋል።.[11] ለሠላሳ ዓመታት ያህል፣ እስከ 2011 ድረስ፣ ሕወሃት በአራት ክልላዊ ፓርቲዎች ገዢ ጥምረት ውስጥ ያልተመጣጠነ ሥልጣን የነበረውን የብሔር ፌዴራሊዝም ሥርዓት ደግፎ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ፖለቲካ ሲቆጣጠር ነበር።[10] በዚህ ጊዜ ውስጥ አንፃራዊ ብልፅግና ቢኖረውም፣ አብላጫ የሆነው የህወሓት ስልጣን በብዙ የሀገሪቱ አካላት ወደ ቅሬታ መርቷል።

ግጭቱ በሰኔ 2013 መጨረሻ ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ስለተባባሰ፣ ይህን ተከትሎ የኢትዮጵያ መንግስት የአንድ ወገን ወይም የተናጠል ተኩስ አቁም አወጀ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ መከላከያ ሰራዊት አካላት ከትግራይ ለቀው ሲወጡ፣ ህወሀት አብዛኛው ክልል በመቆጣጠሩ ፣ ግጭቱ ወደ አፋር (ዞን 2 እና ዞን 4) እና አማራ (ሰሜን ወሎ፣ ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ጎንደር፣ ደቡብ ጎንደር፣ ጠገዴ እና ዋጊመራ) ክልሎች አጎራባች ወረዳዎች ተስፋፋ። በምላሹ፣ የመንግስት አስተዳደር በጥቅምት 23፣ 2014 (በየካቲት 2014 ተነስቷል) በመላ አገሪቱ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጀ፤ በዚህ መሠረት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሚዲያ ተቋማት 'የአሸባሪ ድርጅቶችን' ይደግፋሉ ተብለው ከተጠረጠሩ እስከመታገድ ሊደርሱ ይችላሉ።. በዚህ ምክንያት የሰብአዊ እርዳታ ተዋናዮች በዚህ ጊዜ ወደ ትግራይ ክልል መግባታቸው በመገደቡ የሰብአዊ ፍላጎትን በእጅጉ አባብሶታል።[12,13] ይህ በእንዲህ እንዳለ በታህሳስ 2014 የሕወሃት አካላት ከወጡ በኋላ የኢትዮጵያ ብሔራዊ መከላከያ ሰራዊት የአፋር እና የአማራ ክልሎችን መልሶ መቆጣጠር ችሏል።.[14]

ግጭቱ አሁን ለሁለት ዓመታት ያህል በመቆየቱ በሰው ህይወት፣ በኑሮ እና በህዝብ አገልግሎት እና በመሠረተ ልማት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል።.[15] በሁሉም ተፋላሚ ወገኖች በሰላማዊ ሰዎች ላይ ከባድ የሰብአዊ መብት ረገጣ ተፈጽሟል.[16] በአፍሪካ ህብረት ግፊት ቢደረግም የተኩስ አቁም ድርድር እስካሁን አልቀጠለም። ከመሰረቱ ያለው አለመተማመን ሂደቱን በማደናቀፍ በተዋዋይ ወገኖች ማንኛውንም የውጤት ስምምነት የማክበር እድልን ያዳክማል። የትጥቅ ግጭቶች ድግግሞሽ እና ጥንካሬ ተለዋዋጭና እና አንዳንድ ጊዜ ሊተነብይ የማይችል በመሆኑ ግጭቱ እንደቀጠለ ነው። በትግራይ፣ አፋር እና አማራ ክልሎች የታጠቁ ተዋናዮች ሙሉ በሙሉ መውጣት ባለመቻላቸው ብጥብጥ እና የሰብአዊ መብት ረገጣ አሁንም ስጋት ሆኖ ቀጥሏል።

## ለሰብአዊ ምላሽ ወሳኝ ማህበራዊ አውድ

የሰብአዊ እርዳታ ሰጭዎች ዕርዳታን ለማቅረብ ጥረታቸውን ሲቀጥሉ፣ ውጤታማ እና ሁሉን አቀፍ ምላሽን ለማረጋገጥ ሊያውቋቸው የሚገቡ ቁልፍ የማህበራዊ አውድ ገጽታዎች አሉ።

### ክልሎች እና ብሔረሰቦች

እያንዳንዱ በግጭት የተጠቃው ክልል የበላይ ከሆነው ብሄረሰብ ጋር የተቆራኘ ቢሆንም፣ በተጨማሪም በልሉ የተለያየ ቋንቋ፣ ሃይማኖት እና ሌሎች ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ እና ጂኦግራፊያዊ ሁኔታዎች ያሏቸው የተለያዩ ብሄረሰቦች ይኖራሉ።. ምላሽ ሰጪዎች ስለእነዚህ ማወቅና እና ምላሹን በዚሁ መሰረት ማስተካከል አለባቸው።

**ትግራይ** የኢትዮጵያ ሰሜናዊ ጫፍ ነው። በሰሜን ከኤርትራ፣ በምዕራብ ሱዳን፣ በደቡብ ከአማራ ክልል፣ በምስራቅና በደቡብ ምስራቅ ከአፋር ክልል ጋር ይዋሰናል። የትግራይ ብሄረሰብ የሚገኝበት ቦታ ሲሆን ስሙም ይህን ተከትሎ ተሰይሟል። የትግራይ ህዝብ (እራሳቸውን ተጋሩ ብለው የሚጠሩ) በዋነኛነት አርሶ አደር እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና ተከታዮች ሲሆኑ ከ8-10% የሚሆኑት ሙስሊም.[17]፤ እንዲሁም የፕሮስቲስታንት እና ካቶሊክ እምነት ተከታዮችም ናቸው። የትግራይ ህዝብ ትግርኛ ተናጋሪ ሲሆን፣ ትግርኛ በኢትዮጵያ ውስጥ በሶስተኛ ደረጃ የሚነገር ቋንቋ ነው። በተጨማሪም፣ የትግራይ ክልል አናሳ የኢሮብ እና የኩናማ ቡድኖች መገኛ ነው።[18] እነዚህ ቡድኖች በአገር አቅፍ እና በክልል ደረጃ መደበኛ የፖለቲካ ውክልና ቢኖራቸውም፤ ሙሉ በሙሉ ራስን በራስ የመወሰን ትርጉም ያለው አቅም ስለሌላቸው፤ ቁልፍ መብቶችን ከማስከበር አካያ እና መሰረታዊ አገልግሎቶች ከማግኘት ጉዳይ ብተለይም በኩናማ ጉዳይ ላይ ፈተናዎች ይገጥማቸዋ ። በታሪክ ክልሉ ብዙ ኤርትራውያን ስደተኞችን አስተናግዷል። ምንም እንኳን የተለያየ የብሔር ማንነት ቢኖራቸውም በትግራይ እና አካባቢው ባሉት ክልሎች ብዙ የድብልቅ ብሔር ቤተሰቦች ይኖራሉ።

**በትግራይ ውስጥ ያሉ አናሳ ብሄረሰቦች፡-** ኢሮብ – ከ 30,000 እስከ 40,000 የሚሆኑ ህዝቦች - ከኤርትራ ጋር በሚያዋስነው ከፊል ደረቃማና ተራራማ አካባቢ የሚኖሩ እና በዋነኝነት ካቶሊክ ናቸው። ኩናማዎች በዋናነት በትግራይ ምዕራብ እና ሰሜን ምዕራብ ክልሎች በጋሽ እና ሰቲት ወንዞች መካከል በጋሽ-ባርካ አካባቢ ይገኛሉ። አንዳንድ ኩናማዎች ባህላዊ ሃይማኖታዊ እምነቶችን ይዘው ቢቀጥሉም፣ አብዛኞቹ ወደ ክርስትና ወይም እስልምና ተቀይረዋል። ትግራይ ውስጥ የሚኖሩት ወደ 6000 ሚጠጉ ኩናማዎች ብቻ ሲሆኑ በኢትዮጵያ ከሚገኙት ትናንሽ ብሄረሰቦች መካከል አንዱ ያደርጋቸዋል። ኢሮብ ትግርኛ እና ሳሆ ሲናገሩ ኩናማ የኒሎ-ሳሃራ ቋንቋ ቤተሰብ የሆነውን ኩናማ እና ኢሊት ይናገራሉ።

**አፋር ክልል እና ህዝቡ፡-** የተራራቀ የህዝብ አሰፋፈር ያለው የአፋር ክልል በሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ ይገኛል። በሰሜን ምስራቅ ከኤርትራ፣ በሰሜን ምዕራብ ከትግራይ ክልል፣ በደቡብ ምዕራብ ከኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ከሶማሌ ክልል እና በምስራቅ ከጅቡቲ ጋር ይዋሰናል። አፋር (ወይም ዓፋር) በአፍሪካ ቀንድ የሚኖሩ ሲሆን የኩሽቲክ አፋር እና አረብኛ

ቋንቋዎችን ይናገራሉ.[19] እነዚህ ሕዝቦች አንዳንድ ጊዜ በሌሎች አካባቢዎች የደናኪል፣አዳሊ ወይም ኦዳሊ ሰዎች ይባላሉ፣ነገር ግን እነዚህ ስሞች በአፋር ህዝብ ዘንድ አስጸያፊ ተደርገው ሊወሰዱ ስለሚችሉ ምላሽ ሰጪዎች ሊታቀቡ ይገባል። የአፋር ህዝብ በዋነኛነት በኢትዮጵያ አፋር ክልል እና በኤርትራ እና ጅቡቲ አጎራባች አካባቢዎች የሚኖሩ እና በእንስሳት እርባታ የሚተዳደሩ ድንበር ተሻጋሪ የአርብቶ አደር ማህበረሰብ ናቸው። ይህ ክልል በአፍሪካ ቀንድ ውስጥ በጣም አስቸጋሪ አካባቢ ያለው ሲሆን ከፍተኛ ሙቀት፣ የተዳከመ አካባቢ እና አነስተኛ የውሃ ተደራሽነት አለው።.[20] በአሁኑ ጊዜ ከባድ የድርቅ ሁኔታዎች ከግጭት ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶችን በማወሳሰብ ላይ ናቸው።[21] ወደ 1.3 ሚሊዮን የሚገመት የአፋር ህዝብ በኢትዮጵያ ሲኖር፣ አነስተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ በአጎራባች አገሮች ይኖራል።[22] እነዚህ የኩሽቲክ ሰዎች በዋናነት የሱኒ ሙስሊም ናቸው። የአፋር ማህበረሰብ የሚተዳደረው በጎሳ ስርአት እና በባህላዊ ገዥ በአፋር ሱልጣን ነው። የአፋር ህዝብ በመንግስት የተገለለ እና ተለዋዋጭ አለም አቀፋዊ ማንነት ያለው ቢሆንም፣ አሁን ባለው ግጭት ላይ ጠንካራ ብሄርን መሰረት ያደረገ አቋም ከመያዝ ይልቅ የፌደራል መንግስትን 'አሃዳዊ' ትረካ ወደ ኋላ የመመለስ አዝማሚያ አሳይቷል። [23]

**ድንበር ተሻጋሪ ማህበራዊ ትስስር፡-** በተለይም በትግራይ እና በአፋር ክልል የሚገኙ ብሄረሰቦች፡- በተጋሩ ፣ ኢሮብ፣ ኩናማ እና አፋር ህዝቦችን ጨምሮ በኤርትራ (በአፋር፣ በጅቡቲም ጭምር) ድንበር አቋራጭ የቆየ የጎሳ ግንኙነት አላቸው።[24] በእርግጥ አብዛኛው የኩናማ ህዝብ ኤርትራ ውስጥ ነው የሚኖረው። ይህ የሚያመለክተው በወቅታዊው ቀውስ ወቅት እነዚህ ቡድኖች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ ጠቃሚ ድንበር ተሻጋሪ ትብብር፣ ድጋፍ እና ግብአቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ነው። በእርግጥም የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትን ጨምሮ ባለፉት ግጭቶች ይህን አድርገዋል። ምንም እንኳን ዓለም አቀፍ ድንበሮች እርስ በእርሳቸው እንዲቆራረጡ ቢያደርጉም ግንኙነታቸውን ለማስቀጠል ችለዋል።[24] ግጭቶችና ሌሎች የፖለቲካ ለውጦች ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ ከክልሉ ወደ ሌላ አገር እንዲሜጡ በማድረግ ብዙዎች፣ በተለይም የትግራይ ተወላጆች ከሃገር ዉጭ እንዲኖሩ አድርጓል። የትግራይ ልማት ማህበር ለምሳሌ ጠንካራ የዲያስፖራ ቅርንጫፎች እና ትስስር ያለው መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት በትግራይ ክልል ሰላም ግንባታና ልማት ስራዎችን ለአስርት አመታት ሲሰራ ቆይቷል።.[25] እንደነዚህ ያሉ ቡድኖች እና አለምአቀፍ ኔትወርኮች ግብዓቶች የሚፈሱባቸውን አስፈላጊ መንገዶችን ሊወክሉ እና መደበኛ ምላሽ ሰጪዎች አጠቃላይ የምላሽ ውጤታማነትን ለማስተባበር እና ለማሻሻል ሊያገኟቸዉ ይችላሉ።

**የአማራ ክልል፡-** የአማራ ክልል በሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛው ኢትዮጵያ ይገኛል።[26] በሰሜን ከትግራይ፣ በምስራቅ ከአፋር፣ በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በምዕራብ እና በሰሜን ምዕራብ ከሱዳን እና በደቡብ ከኦሮሚያ ጋር ይዋሰናል። ብዙዉ የክልሉ ህዝብ፣ 91.47% የሚሆኑት የሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪ የአማራ ብሄረሰብ ተወላጆች ሲሆኑ የግብርና ባለሙያዎች እና በመሬት ባለቤትነት ላይ ትልቅ ዋጋ የሚሰጡ ናቸዉ። ሌሎች አብዛኛዎቹ ነዋሪዎች ከሌሎች የኩሽ ቋንቋ ማህበረሰቦች ማለትም አገው/አዊ እና ኦሮሞ፣ ቅማንት እና አገው/ከሚር፣ እና ሌሎች እንደ ቤተ እስራኤል እና አርጎባ ካሉ ቡድኖች የመጡ ናቸው። ክልሉ በጣም ዴሞክራሲያዊ ከሆኑት መካከል አንዱ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ብሄረሰብ የራሱን የአስተዳደር መዋቅር ያስተዳድራል፣ ለአብነትም በአዊ፣ በዋግሕምራ እና በኦሮሞ ልዩ ዞኖች ውስጥ ይታያል። ብዙ ብሔረሰቦች በሚኖሩባቸው ሌሎች ክልሎች እንዲህ ዓይነቱ አሰራር ያልተለመደ ነው። አማርኛ በክልሉ በስፋት የሚነገር ሲሆን አገውኛ፣ህምጥኛ እና አፋን ኦሮሞ በአዊ፣ዋግሕምራ እና ኦሮሚያ ልዩ ዞኖች በቅደም ተከተል ይነገራሉ።.[27] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት በክልሉ ቀዳሚ ሲሆን እስልምና ይከተላል። በግጭቱ መባባስ ዋግሕምራ፣ ሰሜን ወሎ፣ ደቡብ ወሎ፣ ደቡብ ጎንደር፣ ሰሜን ሸዋ እና ሰሜን ምስራቅ ጎንደር ዞኖች በክልሉ ከፍተኛ ጉዳት ደርሰባቸዋል።

## የቀውሱ ማህበራዊ ተፅእኖዎች

ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ መብቶች፡- የጤና፣ በቂ ምግብ፣ ውሃ እና ሳኒቴሽን፣ እንዲሁም የመብራት አገልግሎት፣ የባንክ እና የመገናኛ መሰረተ ልማት የመሳሰሉ መሰረታዊ አገልግሎቶችን የማግኘት መብቶችን ጨምሮ፣ በቀጥታም በግጭቱ እንዲሁም በተዘዋዋሪ አደጋን ሊቀንሱ በሚችሉ እርምጃዎች እጥረት ምክንያት ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዋል። [28] በተለይ ትግራይ ወድማለች።. በክልሉ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የመሠረተ ልማት ንብረቶች ላይ ጉዳት ደርሷል።[5]

## የብሔረሰቦችን አለመግባባት፣ ዘርን ኢላማ ማድረግ እና የአናሳዎች መገለልን ማባባስ

ግጭቱ በብሄሮች መካከል በተለይም በአማራ እና በትግራይ ህዝቦች መካከል ያለውን ውጥረት አባብሷል። ከ2011 ጀምሮ ወደ ትግራይ የሚገቡ የአማራ መንገዶች በአካባቢው ተወላጆች ህወሀት ለረጅም ጊዜ የሀገሪቱን መንግስታዊ የበላይነት በመያዙ እና በአማራ ብሄር ተወላጆች በታሪክ የሚተዳደረውን መሬት በመግዛቱ በመማረራቸው ምክንያት በአካባቢው ነዋሪዎች ተዘግተዋል።.[29] በመሆኑም ግጭቱ ከመጀመሩ በፊት ከአንድ አመት ተኩል በላይ በትግራይ ለሚኖሩ ህዝቦች ንግድ እና ኑሮ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል፤ በመሆኑም ወደ ክልሉ የሚገቡት በቋሚነት ክፍት የሆነው በአፋር በኩል ብቻ ነበር።.[5] የህወሓት ሃይሎች ከአፋር እና ከአማራ ክልል ወደ ትግራይ የሚገቡ የሰብአዊ እርዳታ ኮሪደሮችን በያዙበት ወቅት ውጥረቱ የበለጠ ቀጠለ።.[30] በነዚህ መንገዶች ወደ ትግራይ የሚሄደው ሰብአዊ እርዳታ ሁልጊዜ ለታለመላቸው ሰዎች እንደማይደርስ እና ህወሀት ወጣቶችን በመንጠቅ ወደ ህወሓት ሰራዊት እንዲቀላቀሉ በማድረግ ለቤተሰቦቻቸው ቀለብ እንደሚሰጥ የመንግስት ሚዲያዎች ዘግበዋል።.[31]

አምነስቲ ኢንተርናሽናል እና ሂውማን ራይትስ ዎች ባወጡት ዘገባ፣ የትግራይ ሰላማዊ ዜጎች በአማራ ክልል መንግስት ተዋናዮች በሚመሩ የአማራ ክልል የሚሊሻ ታጣቂዎች እና በብሔራዊ ኃይሎች ተባባሪነት በአወዛጋቢው የምዕራብ ትግራይ ዞን፣ ወደ ትግራይ ከተካተቱት አካባቢዎች አንዱ በሆነው ፣ ዘር የማጽዳት እርምጃ እንደተወሰደባቸው ገልፀዋል። [32] በሌሎች ዘገባዎች፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል የአማራ ብሄር በሆኑት ሰዎች ላይ በህወሓት ጥቃት መፈጸሙን ገልጿል። ይህ ኢላማ በህዳር ወር 2020 በምዕራብ ትግራይ በሚኖሩ ሰላማዊ ዜጎች ላይ የተፈፀመውን እልቂት እና በአማራ ክልል ውስጥ ግድያ፣ መደፈር እና ዘረፋን ያጠቃልላል። ይህ ኢላማ በህዳር ወር 2013 በምዕራብ ትግራይ በሚኖሩ ሰላማዊ ዜጎች ላይ የተፈፀመውን እልቂት [33] እና በአማራ ክልል ውስጥ ግድያ፣ መደፈር እና ዘረፋን ያጠቃልላል።[34]

ተለይተዉ ኢላማ ባይሆኑም በትግራይ ክልል ዉስጥ ያሉት እንደ ኢሮብ እና ኩናማ ያሉ ሌሎች አናሳ ብሄረሰቦችም ከጅምሩ በግጭቱ ውስጥ ገብተዋል። በትግራይ ክልል ውስጥም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ ያላቸው አናሳ ደረጃ፣ እርዳታ ለሚሰጡ ሰብዓዊ አካላት ጨምሮ የማይታዩ እና በጸጥታ ስጋት ምክንያት በእርዳታ ወደ እነርሱ ለመድረስ አስቸጋሪ በመሆኑ ከፍተኛ የምግብ ዋስትና እጦት ሊገጥማቸው ይችላል ተብሎ ይታመናል።[35] ግጭቱ ወደ አፋር እና አማራ ክልሎች በመስፋፋቱ ልጃገረዶች እና ሴቶች በተለይም የአገው/ከሚር፣ የቅማንት (በአማራ ክልል ጎንደር ትንሽ ብሔር) እና በኦሮሞ ብሄረሰቦች ላይ ጉዳት ደርሷል።

## መፈናቀል እና ከስደት ተመላሾች

እስከ የካቲት 2014 ድረስ በመላው ኢትዮጵያ ወደ 4.51 ሚሊዮን የሚገመቱ ሰዎች በአገር ውስጥ ተፈናቅለዋል ተብሎ ሲገመት፣ ግጭት 81 በመቶ ለሚሆኑት ተፈናቃዮች አስተዋፅኦ አድርጓል።[36] በተጨማሪም ወደ 50,000 የሚጠጉ ስደተኞች ወደ ሱዳን የተሰደዱ ሲሆን፣ ይህንንም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ በዘለቀው ከኢትዮጵያ የወጡ ስደተኞች እጅግ የከፋ ነው ሲል ገልፆታል።[37] ሆኖም የመረጃ ክፍተቶች፣የደህንነት ስጋቶች፣የነዳጅ እና የጥሬ ገንዘብ እጥረት፣የግንኙነት መሠረተ ልማት ብልሽት በሰሜናዊው ግጭት ምን ያህሉ እንደተፈናቀሉ [38] ወይም ተፈናቃዮች ምን ዓይነት ፈተናዎች ሊገጥሟቸው እንደሚችሉ በትክክል ለማወቅ አስቸጋሪ አድርጎታል።

**ሠንጠረዥ 1** በአደጋ ጊዜ ጣቢያ ግምገማ ዙር 9 (ጥር-የካቲት 2014) በተጎዱ ክልሎች ላይ ያለውን መረጃ ያሳያል። ይሁን እንጂ እነዚህ አሃዞች በተለይ በአፋር እና በትግራይ ዝቅተኛ ግምት ሊሆኑ ይችላሉ። በተፈጠረው ቀውስ ውስጥ የተፈናቃዮች ቁጥር እና ቦታ እየተቀያየረ እና እየተዘዋወረ ሊሆን ይችላል።

**ሠንጠረዥ 1. ከሰሜን ኢትዮጵያ ክልሎች የተፈናቀሉ ተፈናቃዮች ቁጥር (የካቲት 2014)**

| ክልል | የተፈናቃዮች ብዛት | የተፈናቃዮች መቀመጫ/ጣቢያ ብዛት |
|---|---|---|
| ትግራይ | 1.8 ሚሊዮን | 581 |
| አማራ | 462,529 | 560 |
| አፋር | 175,264 | 83 |

በግጭቱ ወቅት አንዳንድ አካባቢዎች አሳሳቢ ሆነዋል። ለአብነት ያህል በትግራይ ድንበር አካባቢ ለመዳረስ አስቸጋሪ ከሆኑ አካባቢዎች የተፈናቀሉ ተፈናቃዮች በአማራ ዋግ ኽምራ ዞን ቀድሞውንም አስከፊ የሆነዉን ሰብዓዊ ሁኔታን አባብሰዋል።[39] እዚህ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ተፈናቃዮች እንዳሉ ይነገራል፣ ብዙዎቹ በሰቆጣ ከተማ ውስጥ ይገኛሉ። አብዛኞቹ የአገው/ከሚር ብሄረሰብ ተወላጆች ሲሆኑ፣ እንደተጠቀሰው ከትግራይ ተፈናቃዮች ያነሰ ሰብአዊ እርዳታ ትኩረት አግኝተዋል። አካባቢው በተለይ በነዳጅ አቅርቦት ውስንነት እና በተለዋዋጭ የፀጥታ ስጋቶች የተጎዳ ሲሆን ይህም የሰብአዊ ምላሽን በእጅጉ እያስተጓጎለ ነው።[40,41]

ሁኔታው ያልተረጋጋ ሆኖ እያለ በአፋር እና በአማራ ክልል የተፈናቃዮች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል ፣ በተለይም በምስራቅ አማራ 1.5 ሚሊዮን ህዝብ፣ ይህም በከፊል በክልሉ ባለስልጣናት አመቻችነት ወደ ቀድሞ ሁኔታቸው ተመልሰዋል።[36,42] የጸጥታ እጦት እና የመሰረታዊ አገልግሎት እጦት ስጋት ቢያጋጥመውም የተፈናቃዮቹ በድንገትና በተደራጀ መልኩ ወደ አገራቸው መመለሳቸውን የአፋር ባለስልጣናት አስታውቀዋል።.[43] ይሁን እንጂ በአፋር ውስጥ በሚገኙ የትግራይ ተወላጆች ካምፖች ውስጥ በግዳጅ መያዛቸውን የሚገልጹ ዘገባዎችም አሉ።.[44] የምላሽ ጥረቶች በበጎ ፈቃድ የመንቀሳቀስ እና የመመለስ መብትን አፅንዖት መስጠት አለባቸው፣ እንዲሁም  የኑሮ እና መሰረታዊ አገልግሎቶችን ያጡ ከስደት ተመላሾችን ችግር ለመፍታት ያለመ መሆን አለበት።  ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት  የተፈናቃዮች መመለስ በስደተኞች መጠለያ ወይም  ካምፖች ውስጥ እንደ ምግብ እና መጠለያ ባሉ ሀብቶች እጥረት ምክንያት ሊሆን ይችላል።[45]

## ወሲባዊ እና ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት እንደ የጦር መሳሪያ

ኢትዮጵያ ከፍተኛ ወሲባዊና እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች (SGBV) በተለይም የቅርብ አጋሮች ጥቃት (IPV)፣ የሴት ልጅ ግርዛት (FGM)፣ አሁን ካለው ግጭት በፊትም ነበረባት።.[46]  ነገር ግን፣ በግጭት እና መፈናቀል መካከል እንደተለመደው [47] ፣ የሴቶች፣ ልጃገረዶች፣ አካል ጉዳተኞች እና ወንዶች እና ጎረምሶች ልጆች ጭምር ለከፋ ወሲባዊና እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች (SGBV) ተጋላጭነታቸው ተባብሷል። ይህም አካላዊ ጥቃት እና ድብደባ፣ አስገድዶ መድፈር (የቡድን መደፈርን ጨምሮ)፣ ባዕድ ነገርን ወደ ብልት ውስጥ ማስገባት እና አልፎ ተርፎም ሆን ተብሎ በህወሓት፣ ኢትዮጵያ ብሔራዊ መከላከያ ኃይሎች እና በኤርትራ ሃይሎች የተፈፀመ የኤችአይቪ ስርጭት ሪፖርትን ያጠቃልላል።[28] ለዚህ አጭር መግለጫ የተነገሩት ቁልፍ የመረጃ ሰጭዎች ዘገባዎች እንዲሁም የጸሐፊዎቹ በራሳቸው ምላሽ አሰጣጡ ላይ የተመለከቱት ምልከታ እንደሚያመለክተው ግጭት በተከሰተባቸው ክልሎችና ወረዳዎች ሁሉ ጥፋቶች መከሰታቸውን፣ በሁሉም የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሴቶችና ልጃገረዶች በቤት ውስጥም ሆነ ከጦርነት በሚሸሹበት ጊዜ ኢላማ  ተደርገዉ  ጉዳት ይደርስባቸዋል።  ባሎቻቸው ወይም ዘመዶቻቸው (ወይም የተጠረጠሩባቸው) ለተወሰነ ወገን የሚዋጉ ሴቶች በተለይ  በተቃዋሚ ተዋጊዎች ኢላማ ሆነዋል። ከወሲባዊና ጾታዊ ጥቃት ጋር የተያያዘ ጠንካራ መገለልም አለ። አብዛኞቹ ከጥቃቱ የተረፉ ሰዎች ድርጊቱን ለመግለጽ ፈቃደኞች አይደሉም፣ ይህም የተረፉትን ቁጥር ለመገመት አስቸጋሪ ያደርገዋል። አንድ ቁልፍ መረጃ ሰጪ እንዳለችው ከአማራ ቡድኖች ጥቃት አምልጠው  የተረፉት ሰዎች “የጁንታ ትራፊ”  የሚል ስያሜ እደተሰጣቸዉ ተናግራለች።

በእርግጥም አምነስቲ ኢንተርናሽናል እንዳለው አስገድዶ መድፈር እና ጾታዊ ጥቃት በትግራይ ውስጥ የጦር መሳሪያ ሆኖ ያገለገለና ይህም በህይወት በተረፉ ሰዎች ላይ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የአካልና የስነ ልቦና ጉዳት ያደረሰ ነው።[48] በርካታ ቁጥር ያላቸው ሴቶች እና ልጃገረዶች ከተደፈሩ በኋላ ነፍሰ ጡር መሆናቸው እና የጤና መሠረተ ልማት ባለመኖሩ ምክንያት ያልተፈለገ እርግዝና ተሸክመዉ እስከ ወሊድ ድረስ እንዲቆዩ ተደርገዋል። በአንዳንድ አጋጣሚዎች ህጻናትን ጨምሮ የቤተሰብ አባላት የአስገድዶ መድፈር ድርጊቶችን ለማየት መገደዳቸውን የሚገልጹ ዘገባዎች አሉ። ሪፖርቶች በተጨማሪም በሕይወት የተረፉ ሰዎች እና ቤተሰቦቻቸው የጎሳ ስድብ እና የግድያ ዛቻ እንደተፈፀመባቸው ሲገልጹ ወንጀለኞቹ ግን የጠላት ደም ያላቸውን ሴቶች "እያጸዳን" ነዉ ይላሉ ሲሉ ተናግረዋል። ወንጀለኞችም በህይወት የተረፉትን በማገት ለቀናት ወይም ለሳምንታት ለወሲብ ባርነት በማጋለጥ አሰቃቂ ስቃይ ፈጽመዉባቸዋል።[48]

**ለወሲባዊና እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች (SGBV) ምላሽ መስጠት፡-** የወሲባዊና እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች (SGBV) ምላሽን በአጠቃላይ የአደጋ ጊዜ ምላሽ ዉሰጥ ማካተት የምላሽ ሰጪዎች ቁልፍ ትኩረት ነዉ። ወሲባዊና እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን (SGBV) መከላከል እና ስጋትን የመቀነስ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን አከናውነዋል በተጨማሪም የንፅህና መጠበቂያ እና ወሲባዊና እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች (SGBV) መከላከያ ቡክሌቶችን ለሴቶች እና ልጃገረዶች አሰራጭተዋል።  ይህ ስራ ከማህበራዊ  አገልግሎት ጤና እና ልማት ድርጅት (Organization for

Social Service, Health and Development ) ጋር በመተባበር በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በትግራይ ሲሰራ ቆይቷል።[49] በአማራ ክልል በስነ ልቦና የመጀመሪያ እርዳታ (PFA) እና ወሲባዊና እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች (SGBV) በድንገተኛ አደጋዎች ሁኔታ የሰለጠኑ የማህበረሰብ አስተባባሪዎች እና ወሲባዊና እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች (SGBV) ፎካል ሰዎች ተሰማርተዋል[49] በሰሜን ጎንደር ዞን ደባርቅ እና ዳባት ወረዳዎች ወሲባዊና እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች (SGBV) ኬዝ ሰራተኞች ከአማራ ሴቶች ማህበር (አሴማ) ጋር በጥምረት ተሰማርተዋል።.[49]

**የወሲባዊና እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች (SGBV) አገልግሎቶች ቀጣይ ፈተናዎች እና ፍላጎቶች፡-** የጤና ተቋማት መውደም እና የቁሳቁስ እና የጤና አገልግሎት ሰጪዎች እጥረት፣ ተጋላጭ ለሆኑ ህዝቦች በሚሰጠዉ ጥራት ያለው ወሲባዊና እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች (SGBV) አገልግሎት አቅርቦትና እና ተደራሽነት ላይ ተጽእኖ ማሳደሩን ቀጥሏል። በተጨማሪም፣ ቁልፍ መረጃ ሰጭዎች ተጨማሪ የአእምሮ ጤና እና የስነ-ልቦና-ማህበራዊ ድጋፍ አስቸኳይ ፍላጎት እንዳለ አሳስበዋል። ይህ ለስሜታዊ ማገገም እና ከጥቃት ለተረፉ ሰዎች የጋራ ፈውስ፣ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች (SGBV) ብቻ ሳይሆን ለሌሎች በጦርነቱ ለተከሰቱ የስሜት ቀዉስ ለአብነት ያህል እንደ ሌሎች የአመጽ ዓይነቶች፣ መፈናቀል፣ የቤተሰብ መፈራረስ እና መተዳደሪያ መጥፋት የሚፈጸሙ ተግባራትን ይጨምራል።

***ለድጋፍ እና ፈውስ ተስማሚ የሆኑ ተቋማት፡-*** የቁሳቁስ/መሰረተ ልማት እጦት እና ከወሲባዊና እና ጾታን መሰረት ካደረጉ ጥቃቶች (SGBV) የተረፉ ሰዎችን የማጥላላት አውድ አሁን ያሉትን ማህበረሰብ አቀፍ ተቋማት እና ልማዶች መሳብ እና መደገፍ አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታሉ። *ማህበራት በሃይማኖታዊ (በተለምዶ ክርስቲያን) ወይም ባህላዊ ትስስር ላይ በመመስረት የተመሰረቱ አነስተኛ ነጠላ-ፆታ ቡድኖች ሲሆኑ በተለምዶ በየወሩ አንድ ላይ ይሰባሰባሉ።* እንደነዚህ ያሉት ማኅበራት በስሜት ላይ ለሚፈጠሩ ቀውሶች ፈውስ የመስጠት አቅም አላቸው። ማህበር ሴቶች የግል መረጃ የሚለዋወጡበት እና ከእኩዮቻቸው ድጋፍ እና አስተያየት የሚጠይቁበት ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ተብሎ ተለይቷል። ሁኔታዎች በሚፈቅዱበት ጊዜ፣ በማህበረሰብ የሚመሩ ቡድኖች ከሰብአዊ እርዳታ ሰጪዎች የሃብት ድጋፍ በማግኘት በሕይወት ለተረፉ ሰዎች የስነ-ልቦና ድጋፍ የሚተላለፉባቸዉ እንደ አንድ መዳረሻ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ። ሆኖም፣ የተረፉትን ግላዊነት የሚጠብቁ ገለልተኛ አገልግሎቶችም ወሳኝ ናቸው።

በተጨማሪም የሃይማኖት መሪዎች (ለምሳሌ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ቀሳውስት፣ በትግራይ በሰፊው የሚከበሩ) ከወሲባዊና እና ጾታን መሰረት ካደረጉ ጥቃቶች (SGBV) የተረፉ ሰዎችን ለመደገፍ ስለመሰማራታቸዉ ወይም ምን ያህል እንደተሰማሩ ግልጽ አይደለም። የኢትኖግራፊ ጥናት ይህ በወሲባዊና እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች (SGBV) ምላሽ ውስጥ አስፈላጊ ነገርግ ን የጎደለ አካል ሊሆን እንደሚችል ጠቁሟል፣ ምክንያቱም በሕይወት የተረፉ ሰዎች በባህል-ሃይማኖታዊ ምክንያቶች ላይ ግንዛቢያዊ ወይም በጣም እውነተኛ ፣ መገለል ሊደርስባቸው ይችላል።[50] ይህ እንዳይናገሩ ወይም እርዳታ እንዳይፈልጉ ሊከለክላቸው ይችላል። በስልጠና፣ የሀይማኖት መሪዎች መገለልን በመቀነስ፣ የተረፉትን ከተገቢው አገልግሎት ጋር በማስተሳሰር፣ ፈውስ እና ድጋፍን በቀጥታ በማመቻቸት እና በዋናነት፣ በወሲባዊና እና ጾታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች (SGBV) ዙሪያ የአካባቢ ደንቦችን በመቀየር ረገድ ጉልህ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። በ'ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች' ውስጥ ያሉ ሰራተኞች፣ የቤተሰብ ጉዳዮችን እና ሌሎች በትግራይ እና በሌሎች ክልሎች ያሉ የሲቪል ጉዳዮችን የሚዳኙ የመንደር ደረጃ ተቋማት፣ በተፈናቃይ ቦታዎች ላይም ጨምሮ ተመሳሳይ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። እንዲሁም አብዛኞቹ ወንድ በመሆናቸው የተረፉትን እንዴት መደገፍ እንደሚችሉ ላይረዱ ስለሚችሉ ስልጠና እና ግንዛቤ ያስፈልጋቸዋል:.[50] ብዙ ወንዶች ሚስቶቻቸው ወይም ሴት ልጆቻቸው ሲደፈሩ በማየታቸውና የስነልቦና ጉዳት ስለደረሰባቸዉ ተገቢውን አገልግሎት እና ድጋፍ ሊፈልጉ ይችላሉ።

## የመተማመን ቀውስ

የብሔር ብሔረሰቦች ግጭት እና ብጥብጥ በሰሜን ኢትዮጵያ በሚገኙ በርካታ ማህበረሰቦች መካከል ያለው መተማመን እንዲጠፋ ሁኔታ ፈጥሯል። መተማመን በፖለቲካ ደረጃ ደካማ ነው። አንደኛው እይታ መንግስት ህወሀትን (በይፋ አሸባሪ ብሎ የፈረጀውን) በ“ብሄራዊ ውይይት” ወደ እርቅ በሚደረገው ጥረት ውስጥ ለማካተት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ይህ ሁኔታ በታጠቁ እና ባልታጠቁ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል፣ ህዝብ እና የሃይማኖት መሪዎች ያለውን ተቀባይነት በመጉዳት ዘላቂ እና ሁሉን አቀፍ ሰላም የመፍጠር እድልን ይቀንሳል። [51]

ፅንፍ በያዘ እና ደካማ የፖለቲካ አመኔታ ውስጥ፣ የሰብአዊ ምላሽ ሰጪዎች ከፖለቲካ ቡድኖች ጋር በተለይም በሰላማዊ ሰዎች ላይ ከሚፈጸሙ አሰቃቂ ወንጀሎች ጋር ከተያያዙት ጋር እንዳይሰለፉ ወይም እንዳይመስሉ መጠንቀቅ አለባቸው። በሚቻልበት ጊዜ እና ቦታ ሁሉ፣ ከታመኑና ከሁከት ከራቁ የአካባቢ ኔትወርኮች፣ ተቋማት እና ሲቪል ማህበረሰብ (አንዳንዶቹ ከብሔር ጋር የተገናኙ ሊሆኑ ይችላሉ) በቀጥታ መሳተፍ ቁልፍ አገልግሎቶችን እና ድጋፎችን ለማቅረብ

ውጤታማ መንገዶች ሊሆኑ ይችላሉ። በተለይም የጎሳ እና የፖለቲካ መስመሮችን የሚያቋርጡ የሃይማኖት መሪዎችን እና መረቦችን ሚና መጠቀም በጣም አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ብዙ ቤተሰቦች እና ማህበረሰቦች ውስጥ ከመደበኛ ህጎች ወይም ተቋማት የበለጠ ጠንካራ ሚና ሊጫወት ይችላል። የሃይማኖት መሪዎች በቤተሰብ፣ በማህበረሰብ እና በክልል ደረጃ የሰላም ግንባታ ጥረቶችን እንደ ሽምጋይ ሆነው መስራት ይችላሉ።[52] እንደተጠቀሰው፣ የሃይማኖት መሪዎች ከወሲባዊና እና ጾታን መሰረት ካደረጉ ጥቃቶች (SGBV) የተረፉ ሰዎችን በማማከር፣ የማህበረሰቡን ድጋፍ በማጠናከር እና አግላይ ባህሪን እና የወንጀል ድርጊቶችን በማውገዝ የበኩላቸዉን ሚና መጫወት ይችላሉ።

ሌሎች የአካባቢ ተቋማት እና በብዙ ብሄረሰቦች የሚገኙ ባህላዊ ማህበራት በአካባቢ ደረጃ ለተጎዱ ሰዎች ድጋፍ እና ሰብአዊ እርዳታን ሊያመቻቹ ይችላሉ። እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ:

1. *እድር* - አባላት ወርሃዊ የገንዘብ መዋጮ በማድረግ በአደጋ ጊዜ የሚጠቀሙበት ባህላዊ የበጎ ፈቃድ ማህበር ነዉ። እድሮች በግጭቱ በተጎዱ ብዙ ማህበረሰቦች ውስጥ አሉ፣ ነገር ግን አንዳንዶቹ ምላሽ እና የማገገሚያ ጥረቶችን ለመደገፍ ከሌሎቹ የበለጠ የገንዘብ ምንጭ ሊኖራቸው ይችላል።
2. *እቁብ* - ህይወታቸውን እና የኑሮ ሁኔታቸውን ለማሻሻል በትናንሽ ሰዎች ስብስብ ዉስን ወርሀዊ ገንዘብ በማዋጣትና በየተራ ለአባላት ጠቀም ያለ ተዘዋዋሪ ገንዘብ ለማቅረብ የተቋቋመ ማህበር ነዉ። [53] እቁቦች በተመሳሳይ መልኩ ምላሽ ሰጪዎች በማህበረሰብ ደረጃ እርዳታ እና ድጋፍ ለመስጠት የሚሳተፉበት መንገዶች ሊሆኑ ይችላሉ።.

ቀውሱ በነዚህ ተቋማት ህልውና ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር እንደሚችል ልብ ማለት ያስፈልጋል። ምላሽ ሰጪዎች የሚሰሩ እድሮችን፣ እቁቦችን እና ሌሎች የታመኑ እና በአካባቢው ስር የሰደዱ ተቋማትን እና ኔትወርኮችን በመለየትና ተሀድሶአቸውን በመደገፍ ፣የተቸገሩ ሰዎችን በመደገፍ ረገድ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴያቸውን ማጎልበት ይችላሉ።

## ጤና፣ የጤና ስርዓት ተፅእኖዎች እና ጤናን የመፈለግ ባህሪ

ግጭቱ በአፋር፣ በአማራና በትግራይ ክልሎች የጤና፣ የትምህርት፣ የውሃ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የመብራት እና የባንክ መሰረተ ልማቶችን ዘረፋና ውድመት አስከትሏል።[28]ይኸ የግንኙነቶች መቋረጥ እና ሙሉ በሙሉ የኤሌክትሪክ መቆራረጥ ምላሽ ሰጪዎች ምን እየተፈጠረ እንዳለ በትክክል የመረዳት እና ተፅእኖዎችን የመቀነስ አቅማቸው ውስን እንዲሆን አድርጎታል።[54]

**ጤና እና የጤና ስርዓት ተፅእኖዎች፡-** ኢትዮጵያ ባለፉት አስር አመታት በጤና ስርአቷ ላይ በተለይም ጤና ኬላዎችንና ጤና ጣቢያዎችን እና የሰለጠነ የሰው ሀይል በማቋቋም ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ አፍሳለች።[55,56] ይህ መሠረተ ልማት በተለይም በጦርነት በምትታመሰው ትግራይ ላይ በግጭቱ ክፉኛ ተጎድቷል። ይህ የሆነው ሆን ተብሎ የጤና ተቋማትን በማውደም፣ በመዝረፍ፣ አልፎ ተርፎም በታጣቂዎች በማስወረር እና ከጦርነቱ ጋር በማገናኘት ወሳኝ የአቅርቦት እጥረት እንዲፈጠር ለማድረግ ወደ ክልሉ የሚገቡ የመሬት መንገዶችን በመዝጋት ነው።[49,57] ለምሳሌ በትግራይ 27.5% ሆስፒታሎች፣ 17.5% ጤና ጣቢያዎች እና ከ712 ጤና ኬላዎች መካከል አንዳቸውም ጦርነቱ ከጀመረ እስከ 6 ወራት ሙሉ ለሙሉ አገልግሎት መስጠት አልቻሉም።[54] በተጎዱ አካባቢዎች ነዳጅ ባለመኖሩ የተንቀሳቃሽ ወይም ሞባይል ጤና ክፍሎች ሥራ ላይ እንቅፋት ፈጥሯል።.[49] በጤና ባለሙያዎች ላይ ከሚደርሰው ከፍተኛ ስራ ማቋረጥና መፈናቀል ጋር ተያይዞ እንደ የእናቶች እና ህፃናት ጤና አገልግሎት ያሉ ወሳኝ አገልግሎቶች አቅርቦት ቀንሷል በተጨማሪም የተመጣጠነ ምግብ እጥረት እና ተላላፊ እና ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ተባብሰዋል።[54,58–60] በዲያስፖራ ኔትወርኮች ውስጥ ያሉ የጤና ባለሙያዎች - ለምሳሌ HPN4ትግራይ ድርጅት ትልቅ ዝርዝር ዉስጥ ያሉት - አገልግሎቶችን በቀጥታ ለማቅረብ ጓጉተው በመጠባበቅ ላይ ናቸው።።። ነገር ግን አክቲቪስት ወይም አሸባሪ ተብለው በመንግስት እንዳይታሰሩ በመፍራት ወደ ሀገር እንዳይገቡ ተደርገዋል።

በመቐለ ከተማ ግንባር ቀደም በነበረ ሆስፒታል እንዴት በአቅርቦትና በሰው ሃይል እጥረት ምክንያት ማዳን እየተቻለ ህሙማንን ወደ ቤታቸው ሄደው እንዲሞቱ ለመላክ እንደተገደደ አስተያየት ሰጪዎች ጠቁመዋል።[61] በተጎዱ አካባቢዎች ብዙዎች ያጋጠሟቸው ጭካኔዎች እና መከራዎችም ከባድ የአእምሮ ጤና ችግሮች ስጋት ፈጥሯል። በአፋር እና በአማራ ክልሎች ለሥነ ልቦና ጉዳት እና ሌሎች ችግሮች አስቸኳይ የአእምሮ ጤና ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል ተብሎ የሚገመተው 30,000 የሚጠጉ ሰዎች አሉ።[62] በጤና ስርአት መሠረተ ልማት እና በሰዎች ጤና ላይ የሚደርስ ጉዳት በተጨማሪም ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ እና ትኩረት የሚሹ የረጅም ጊዜ መዘዞች አሉት።

**ለጤና አገልግሎት አቅርቦት ግንዛቤዎች፡-** የተጎዱ ህዝቦች የጤና ፍላጎቶች እየተባባሰ ቢመጣም፣ በግጭቱ እና በጤና ስርዓቱ ውድመት ውስጥ ሰዎች እንዴት የጤና እንክብካቤን እንደሚፈልጉ ወይም እንደሚያገኙ በተመለከተ ያለዉ ማስረጃ ጥቂት ነዉ። ግጭቱ ግን አንዳንድ ሰዎችን የጤና አገልግሎት ለማግኘት አደገኛ ጉዞ እንዲያደርጉ ያደረጋቸው ሲሆ ለምሳሌ በምዕራብ ትግራይ የተያዙ ቦታዎችን አቋርጠ ሱዳን ድረስ እንዲሄዱ አድርጓቸዋል። ከግጭቱ በፊት የተገኙት ማስረጃዎች መስራት የሚችሉ አገልግሎቶች በጣም ውጤታማ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ለሚፈልጉ ምላሽ ሰጪዎች የተወሰነ ግንዛቤን ይሰጣል። በትግራይ እና በአማራ የተደረገ ጥናት ለብዙ የተለመዱ በሽታዎች ባዮሜዲካል እንክብካቤ እና ለህፃናት ህመም  የቅድመ  ጥንቃቄ ጤና ፍለጋ በሁሉም ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ቡድኖች ውስጥ ከሞላ ጎደል ሁለንተናዊ ምርጫ አሳይቷል።[55] የአዋቂዎች ጤና ፍላጎት ግን በማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የበለጠ የተወሰነ እንደሆነ ታይቷል፣ ከድሃ ቤተሰቦች የመጡት ደግሞ እንክብካቤ ፍለጋን የማዘግየት እድላቸው ሰፊ ነው።[55] ከግጭቱ እና ከኢኮኖሚያዊ ሀብቶች ከፍተኛ መመናመን አንፃር፣ ይህ በይበልጥ ጎልቶ የሚታይ ሊሆን ይችላል፣ ይህም የሞባይል ጤና አሃዶችን እና ምንም ወጪ የሌለበት እንክብካቤ አቅርቦትን ወሳኝ ያደርገዋል። በተጨማሪም፣ የባዮሜዲካል እንክብካቤ በሰፊው ተቀባይነት ቢኖረውም፣ እፅዋትን የሚያካትቱ አገር በቀል እና ሃይማኖታዊ የፈውስ ልማዶች፣ [63] ጸሎት ወይም ፀበል እንዲሁ ተወዳጅ እና ምናልባትም የበለጠ ተደራሽ ሊሆን ይችላል። የሀይማኖት ተቋማት እና ፈዋሾች ስለ በሽታ ግንዛቤ እና የሰዎች እንክብካቤ የመፈለግ ልምዶች ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ። ምላሽ ሰጭዎች ይህንን አውቀው ወሳኝ የባዮሜዲካል እንክብካቤን ተደራሽ ከማድረግ በተጨማሪ፣ባዮሜዲካል ካልሆኑ ፈዋሾች ጋር አግባብነት ባለው ጊዜ መስራት አለባቸው። ከሃይማኖት አንፃር እንክብካቤ ፍለጋ ላይም ልዩነቶች ሊኖሩ ይችላሉ። የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ቤተሰቦች ከሙስሊም ቤተሰቦች በተሻለ የባዮሜዲካል እንክብካቤን  ሲፈልጉ ተስተውለዋል።[55,64] ጾታን ጨምሮ ሌሎች ጉዳዮችም አስፈላጊ ሊሆኑ ይችላሉ። ለአብነት ያህል የጤና ባለሙያዎች ጾታ በአፋር ክልል ውስጥ ባሉ ማህበረሰቦች ውስጥ የጤና ፈላጊ ባህሪ ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ታይቷል። ነፍሰ ጡር ሴቶች በምጥ ጊዜ እና በወሊድ ጊዜ ከወንዶች የጤና ባለሙያዎች ጋር አካላዊ ንክኪን ለማስወገድ በሚል ወደ ተቋማት ለመሄድ ፍቃደኛ ሊሆኑ አይችሉም።[65]

## በወጣቶች ላይ ያለ ተጽእኖ

በአጠቃላይ፣ ግጭቱ በወጣቶች ላይ በሚያደርሰው ተጽእኖ ላይ ማስረጃዎች የተገደቡ ናቸው፣ በመሆኑም ወጣቶች በአግባቡ መደገፋቸውን ለማረጋገጥ ተጨማሪ መረጃ በጣም አስፈላጊ ነው።

**ትምህርት፡-** በአገር አቀፍ ደረጃ ወደ 8,700 የሚጠጉ ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ተጎድተዋል፣ ይህም 2.9 ሚሊዮን ህጻናትን ወይም 17 በመቶ እድሜዉ ለትምህርት የደረሰውን የሀገሪቱን ህዝብ ይጎዳል። ከተጎዱት ትምህርት ቤቶች 70 በመቶ የሚሆኑት  የሚገኙት በትግራይ፣ አፋር እና አማራ ክልሎች ነዉ።[43] ይህ የሚያሳየው ትምህርት ማጣትን ብቻ ሳይሆን በክልሉ ከፍተኛ የምግብ ዋስትና እጦት ባለበት ወቅት በትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራሞች በኩል የሚደረገዉን የምግብ አቅርቦትን ማጣትንም ጭምር ነው። መምህራንም ትምህርት ቤቶችን ክፍት የማድረግ ችሎታቸውን የሚነኩ ከፍተኛ ግላዊ ችግሮች ሊያጋጥሟቸው ይችላል። የምግብ እጦት እና የገቢ ማጣት ችግርን ለመቋቋም ለሚታገሉ አባወራዎች አሉታዊ የመቋቋሚያ ስልቶች ማለት ህጻናትን በዝባዥ ሁኔታዎች ውስጥ እንዲሰሩ እና የትምህርት አገልግሎቶች ቢኖሩም ከትምህርታቸው እንዲርቁ ማስገደድ ማለት ሊሆን ይችላል።[66]

**ያለ-ዕድሜ ጋብቻ፡-** ኢትዮጵያ በአለም አቀፍ ደረጃ  **ያለ-ዕድሜ ጋብቻ**  ከፍተኛ ቁጥር ካላቸው ሀገራት አንዷ ስትሆን ሰሜን ኢትዮጵያም ከዚህ የተለየ አይደለም። በድርቅ ምክንያት ቤተሰቦች ከፍተኛ የምግብ እጦት ችግርን ለመቋቋም በሚታገሉበት ሂደት፣ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ያለ እድሜ ጋብቻ በአንድ አመት ውስጥ በእጥፍ ጨምሯል[67]።  በሰሜን ኢትዮጵያ ያለዉ ተመሳሳይ የምግብ ዋስትና እጦት እና የትምህርት ማጣት ጭንቀት ለልጅነት ጋብቻ ተጨማሪ አደጋዎች ናቸው።  የሰብአዊ ምላሽ ንቁ፣ ጥንቃቄ የተሞላበት እና ከዋና ዋና የሀገር ውስጥ ተዋናዮች እና አውታረ መረቦች፣ እንደ መምህራን እና የሴቶች ማህበራት እና ቢሮዎች ጋር አብሮ በመስራት በአደጋ ላይ ያሉ ልጃገረዶችን እና አባወራዎችን መለየትና መደገፍ አለበት። [68]

**የአእምሮ ጤና ስጋቶች፡-** ግጭቱ፣ የጥቃት መፈፀምን ጨምሮ፣ በልጆች እና ወጣቶች ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ሊያሳድር እና ለደህንነታቸው እና ለህይወት እድላቸው የረጅም ጊዜ መዘዝ ሊያስከትል ይችላል። በትግራይ 122 ታዳጊ ወጣቶች ላይ የተደረገ አንድ የጥናት ግኝት እንዳሳየዉ፣ ግጭቱ ሊጀመር አካባቢ እና  ግጭቱ ከተጀመረ አጭር ጊዜያት መካከል የጭንቀት ልምዶች በሶስት እጥፍ እና የመንፈስ ጭንቀት ከ16% ወደ 25% ከፍ ብለዋል። [69]

**የግጭት ቀጥተኛ ተጠቂዎች፡-** ወጣቶች በቀጥታ የግጭት ሰለባ ይሆናሉ፣ ለምሳሌ ለግዳጅ ወታደሮች ወይም የጦር እስረኞች። አንዳንዶች ግጭትን ሲሸሹ በኮንትሮባንዲስቶች ሰለባ ሊወድቁ ወይም የጠላት ተዋጊዎች ወይም ሰርጎ ገቦች ተብለው ሊከሰሱ እና ከዚያም ሊታሰሩ ይችላሉ።

## የምግብ ዋስትና ማጣት መጨመር

በመላው ኢትዮጵያ በተከሰቱት አስከፊ ተደራራቢ ቀውሶች እና የድርቅ አደጋዎች የተመጣጠነ ምግብ እጥረት እና የምግብ ዋስትና እጦት ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ ላይ እየደረሰ ነው። ምንም እንኳን ምግብ እና ሌሎች ቁሳቁሶችን የጫኑ የሰብአዊ ኮንቮይዎች በአሁኑ ጊዜ በግጭት ወደተጎዱ አካባቢዎች በየብስ መንገድ መድረስ ቢችሉም (በአየር የሚደረጉ ወሳኝ አቅርቦቶች ቢቀጥሉም)፣ [70] በሰሜን ኢትዮጵያ 13 ሚሊዮን ሰዎች የምግብ ዕርዳታ ሲፈልጉ፣ ከሰባት እስከ ስምንት ሚሊዮን የሚደርሱት ለከፋ አጣዳፊ የምግብ ዋስትና ማጣት እየተጋለጡ ነው።[3]

**በግብርና ላይ ተጽእኖ፡-** ለምግብ እጦት አስተዋጽኦ ከሚያደርጉት ቁልፍ ነገሮች አንዱ የእርሻ እንቅስቃሴ መቋረጥ ነው። በትግራይ ውስጥ በ 2013 በተፈጠረው ግጭት 75% የሚሆነው የክልሉ ህዝብ ኑሮዉን የተመሰረተበት እና ለብዙወች የህይወታቸዉ ማቆያ የሆነዉ የማረስ፣ የመትከል እና ሌሎች የእርሻ ስራዎች ምን ያህል እንደተጎዱ ተመራማሪዎች አሳይተዋል። እነዚህ ተጽኖዎች የግብርና ግብአቶች የመኖርና እና እነሱን የማግኘት እጥረትን፣ በመትከል ላይ ወታደራዊ ጣልቃ ገብነትን፣ የግብርና መሳሪያዎችን ማውደምን ወይም መዝረፍን እና የማረሻ እንስሳትን መግደልን ያካትታሉ። ብዙ ወንድ ገበሬዎችም በወታደሮች እንዳይገደሉ በመፍራት ሽማግሌዎች፣ ሴቶች እና ህጻናት የእርሻ ስራ እንዲሰሩ በመተዉ ሸሽተዋል ወይም ተደብቀዋል።[71] ቀጣይነት ያለው የጸጥታ ችግር እና መፈናቀል በክልሉ ግብርና ላይ ተጽእኖ ማሳደሩን መቀጠሉ አይቀርም። ማብቀል በሚቻልበት ቦታ እንኳን፣ አንዳንድ አርሶ አደሮች ከተለያዩ የምግብ ሰብሎች ይልቅ በእህል ላይ ትኩረት ማድረጋቸዉን ተናግረዋል። ምንም እንኳን የሚጠቀሙት የሰው ጉልበት አነስተኛ ቢሆንም፣ ጥራጥሬዎች በአልሚ ምግብ ይዘታቸዉ ከአትክልትም ያነሱ ናቸው።[71] ሰዎች ወደ ቤታቸው መመለስ በሚችሉበት ጊዜ እና ቦታ፣ የግብርና ስራን ለማስቀጠል የሚደረገው እርዳታ ወሳኝ ይሆናል። ይሁን እንጂ በድርቅ ሁኔታዎች ተጎድቶ ሊሆን ስለሚችል ፣ የምግብ ምርት ለማገገም የተወሰነ ጊዜ ይወስዳል። የምግብ እና የተመጣጠነ ወይም አልሚ ምግብ እርዳታ ለተመላሾች መሰጠቱ መቀጠል አስፈላጊ ነው።

**ለምግብ እጦት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ሌሎች ምክንያቶች፡-** የግብርና መቆራረጥ፣ ሌሎች የመተዳደሪያና የገቢ ማስገኛ እድሎች መጥፋት ፣ የምግብ ዋጋ መናር፣ የገበያ ተደራሽነት ውስንነት [72] እና መፈናቀል ሁሉም በአንድ ላይ በክልሉ የምግብ ዋስትና እጦት አስተዋጽኦ አድርገዋል። የተፈናቃዮች ማእከላት ለመድረስ ረጅም ርቀት መጓዝ ያለባቸው ሴቶች እና ልጃገረዶች ይበልጥ በምግብ እጥረት የተጠቁ ናቸው። ይህ የምግብ እና ሌሎች ሀብቶችን ተደራሽነት በሚቆጣጠሩት ሰዎች የሚደርስባቸውን ወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃትን ጨምሮለሌሎች አደጋዎች ተጋላጭነታቸውን ይጨምራል።

**አሉታዊ መቋቋም፡-** የምግብ ዋስትና እጦት ብዙዎች በሕይወት ለመትረፍ በአሉታዊ የመቋቋሚያ ስልቶች ውስጥ እንዲሳተፉ አድርጓቸዋል። እነዚህ ቁጠባዎችን እና ሀብቶችን ማሟጠጥ፣ በጤና እና በትምህርት ላይ የሚወጣውን ወጪ መቀነስ እና በቤተሰብ እና በማህበራዊ አውታረመረቦች ላይ ጥገኝነት መጨመርን ሊያካትቱ ይችላሉ። እንደተጠቀሰው፣ አንዳንዶች ምግብ ለማግኘት ተዋጊ ኃይሎችን እንዲቀላቀሉ ተገድደዋል፣ ሌሎች ደግሞ ወደ ወሲባዊ ንግድ እና/ወይም ግብይት እንዲገቡ ተገፋፍተዋል። ከሌሎች የኢትዮጵያ አካባቢዎች በተፈናቀሉ ታዳጊ ወጣቶች ላይ የተደረገ ጥናትም ወጣቶች ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ለመመገብ ዝቅተኛ ደመወዝ የሚያስገኙ ስራዎችን ለመስራት ሊገደዱ እንደሚችሉ ተጠቁሟል።[66] ከመልሶ መቋቋም ይልቅ፣ እንደዚህ አይነት ስልቶች ዘላቂነት የሌላቸው እንደሆኑ ታዉቀዉ፣ የሰብአዊ ምላሽ ሰጪወች እነዚህን ለመጠቀም ያለ ፍላጎትን ለመገደብ ያለሙ መሆን አለባቸው።

## የውሃ እና የንፅህና ገልግሎቶች ተደራሽነት

**ጉልህ የውሃ እና የንፅህና ፍላጎቶች፡** በቂ እና ንፁህ ውሃ የማግኘት መሰረታዊ መብት በኢትዮጵያ ህገ መንግስት የተደነገገ ነው።[4] ሆኖም በ2014 ከፍተኛ የሆነ የሰብአዊ ዉሃ እና ንጽህና አጠባበቅ ፍላጎቶች እንደሚኖሩ ተተንብየዋል፣ በዚህም 16.2 ሚሊዮን ሰዎች እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው ተለይቷል።[73] በሰሜን ኢትዮጵያ በተፈናቀሉ አካባቢዎች በቂ የዉሃ እና ንጽህና አጠባበቅ አገልግሎት መስጠት የበሽታዎችን እና የተመጣጠነ ምግብ እጥረትን ለመከላከል ወሳኝ ነው።[74] ምንም እንካን ከሰኔ 2012 ጀምሮ የውሃና ንፅህና ፈጣን ምላሽ ዘዴ አጋሮች 1.4 ሚሊዮን ተፈናቃዮችን ተደራሽ ቢያደርጉም እና የውሃ እና ሳኒቴሽን አገልግሎት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን ቢያስተናግዱም፣[75] በአብዛኛዎቹ የተፈናቃዮች ማእከላት የውሃ እና ንፅህና አገልግሎት አሁንም በቂ አይደለም።[76]

**ዉስን የስርዓተ-ፆታ ስሜታዊነት፡-** በፈጣን የውሃ በታወች ግንባታ እና የውሃ ማጠራቀሚያዎች አቅርቦት ላይ ያተኮረዉ ምላሽ በዉሃ እና ንጽህና መሠረተ ልማት ላይ ያሉ የሥርዓተ-ፆታ ጥያቄዎችን ለመፍታት ወጥነት የጎደለው ነው። በሥርዓተ-ፆታ ሚና ምክንያት ሴቶች እና ልጃገረዶች ውሃ ለመቅዳት ረጅም ርቀት በመጓዝ ለምግብ ማብሰያ እና ጽዳት ዓላማዎች በተለይም በደረቅ ወቅት በጥንቃቄ መከፋፈል አለባቸው። ይህ ሴቶች እና ልጃገረዶችን ለወሲባዊና እና ጾታን መሰረት ላደረጉ ጥቃቶች (SGBV) ስጋት የሚያጋልጥና እና በትምህርታቸዉ ወይም ሌሎች ተግባራት ላይ የመሳተፍ ችሎታቸውን የሚገድብ ነዉ። እንደ የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ ዕቃዎች አቅርቦት፣ ሽንት ቤት በሚጠቀሙበት ወቅት ግላዊነት እና ደህንነት በመሳሰሉት በንፅህና አጠባበቅ ዙሪያ ያሉ ፍላጎቶቻቸው በተለይም በዋና የጦርነቱ ወቅት ከፍተኛ ትኩረት ተነፍጓቸዋል።.[77–79]

**ወቅታዊነት ስጋቶች፡-** ዝናባማ እና ደረቅ ወቅቶች በተፈናቃዮች ካምፖች ውስጥ በውሃ እና በንፅህና ላይ ተግዳሮቶችን እና አደጋዎችን ይፈጥራሉ። በዝናብ ጊዜ ግቢዎቹ ጭቃ ሊሆኑ ስለሚችሉ ሰዎች በተለይም ህጻናት፣ አዛውንቶች እና አካል ጉዳተኞች ለመጓዝ ወይም ለመንቀሳቀስ አስቸጋሪ ያደርግባቸዋል። የዉሃ እና ንጽህና መሠረተ ልማት እና የውሃ ጥራት ሊበላሹ ወይም ላይስማሙ ይችላሉ። ለኮሌራ፣ ለተቅማጥ እና ለሌሎች ህመሞች የሚያጋልጡ በሽታዎችም እንደዚህ ባሉ ሁኔታዎች ሊጨምሩ ይችላሉ።[80]

## ሰላምን እና መቋቋምን መደገፍ

በግጭት ለተጎዱ ማህበረሰቦች አስቸኳይ ሰብአዊ ፍላጎቶች መሟላት አስፈላጊ ቢሆንም፣ የሚመለከታቸው ምላሽ ሰጪዎች ለሰላም ግንባታ ጥረቶች እና ለዘላቂ ማገገምና ልማት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ማድረጋቸው አስፈላጊ ነው። ይህ በማህበረሰብ መር የግጭት አስተዳደር እና ሰላም ግንባታ ላይ የሚደረገዉን ቀጣይነት ያለው እና ተጨማሪ ኢንቨስትመንት ማካተት አለበት።[81] በ2011 የወጣዉ አዲስ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት (ሲኤስኦ) ህግ የውጭ እና የሀገር ውስጥ የሲቪል ማህበራት በአስተዳደር እና ሰላም ግንባታ ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ እና ለእነዚህ እና ሌሎች ተግባራት ከውጭ የሚገኘውን ገንዘብ እንዲጠቀሙ ፈቅዷል። ሆኖም፣ መንግስት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች 'አሸባሪ' ተብለው ከተሰየሙ ድርጅቶች ጋር እንደሚገናኙ ከገመተ ፈቃዳቸዉ በመንግስት ሊሰረዝ የሚችልበት ስጋት እንዳለ ነዉ።

የሰላም ግንባታ ጥረቶች ሁሉን አቀፍ እና ዓላማ ያላቸዉ በመሆን፣ የተጋላጭ ወገኖችን ድምጽ መስማት እና ያሉትን የሰላም ግንባታ ተግባራት በአከባቢ ደረጃ መጠቀም አለባቸው። ይህ በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ተጋላጭ ማህበራዊ ቡድኖችን እና የአስተያየት መሪዎችን ማሰስ እና ሁሉም ተሳታፊ እና ተደማጭ የሚሆኑበት መንገድ የሚረጋገጥበትን ጥረት ማገዝ ይፈልጋል። ለምሳሌ በአፋር ክልል በማህበረሰብ አቀፍ ደረጃ ውሳኔ ሲደረግ የጎሳ መሪዎች ተፅእኖ ፈጣሪ ሲሆኑ ሴቶች፣ ወጣቶች እና አካል ጉዳተኞች ብዙ ጊዜ አይካተቱም። የባህል ተቋማት እና ሀገር በቀል የመግባቢያ ልማዶች ከተወሰኑ ቡድኖች ጋር ለመቀራረብ እድሎችን ሊሰጡ ይችላሉ። ለምሳሌ *ዳጉ* በመባል የሚታወቀው ባህላዊ ትውፊት በብሔረሰቡ አባላት የሚደረግ የቃል፣ የሥርዓተ- የመግባቢያ መንገድ እና የአፈጻጸም ዘዴ መቋቋምን ለመደገፍ ሊጠቅም ይችላል።[82] ከትግራይ ክልል ምስራቃዊ ክፍል ሌሎች ምሳሌዎች ብንወስድ *አዳር* (የቃል ግጥም አይነት)፣ *ጓይላ* (ዘፈን እና ውዝዋዜ) እና ምሳሌያዊ አባባሎች ይካተታሉ።[83]

ከግጭት በኋላ የሚያገግሙ አገልግሎቶችን፣ መሠረተ ልማቶችን እና ተቋማትን በዘላቂነት ለማገዝ የሀገር ውስጥ አቅምን በገንዘብ ማገዝ እና መደገፍ አስፈላጊ ነው። ይህ ለግጭቱ እና ለተደራራቢ ቀውሶች የረዥም ጊዜ ውጤቶች ሊሆኑ የሚችሉትን የማህበረሰቡን የመቋቋም አቅም ከፍ ሊያደርግ ይችላል። በወረዳ ደረጃ፣ የአቅም ማጎልበቻ ተግባራትን በነባሩ የሀገር ውስጥ የመንግስት ሰራተኛ የሰው ሃይል ላይ በማተኮር፣ መደበኛ የስራ ሂደቶችን መሻሻል መደገፍ (ለምሳሌ በፍጥነት የሀብት ማሰማራት አቅምን ጨምሮ) እንዲሁም ከሰዎች እና ማህበረሰቦች ጋር አካታች በሆነ መንገድ መሳተፍ ይቻላል። በቀበሌ ደረጃ ጥረቶቹ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ የማህበረሰብ መዋቅሮችን ለምሳሌ ማህበረሰብ አቀፍ አደረጃጀቶችን በማጠናከር የአካባቢ መፍትሄዎችን መደገፍ ላይ ትኩረት ማድረግ አለባቸው።[84]

## REFERENCES


1. UNICEF Ethiopia. (n.d.). *Humanitarian Action for Children (HAC)*. Retrieved 3 May 2022, from https://www.unicef.org/media/112126/file/2022-HAC-Ethiopia.pdf
2. World Food Programme. (2021). *Ethiopia Annual Country Report 2021 Country Strategic Plan 2020—2025*. https://docs.wfp.org/api/documents/WFP-0000138025/download/?_ga=2.31374911.1882648533.1651567258-1700548338.1651567258

3. USAID. (2022). *Ethiopia—Northern Ethiopia Crisis Fact Sheet, JUNE 2022* (Fact Sheet #7). USAID. https://reliefweb.int/report/ethiopia/ethiopia-northern-ethiopia-crisis-fact-sheet-7-fiscal-year-fy-2022
4. Federal Democratic Republic of Ethiopia. (1995). *Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia*. National Legislative Bodies / National Authorities. https://www.refworld.org/docid/3ae6b5a84.html
5. Ethiopia Insight. (2022, May 13). *Ethiopia: Tigray's economy destroyed by civil war*. https://www.theafricareport.com/203234/ethiopia-tigrays-economy-destroyed-by-civil-war/
6. International Crisis Group (ICG). (1 February). *Eight priorities for the African Union in 2022* (p. 20). International Crisis Group. https://www.crisisgroup.org/africa/african-union-regional-bodies/b-177-eight-priorities-african-union-2022
7. Neuman, S. (2021). *9 Things to Know About The Unfolding Crisis In Ethiopia's Tigray Region*. https://www.npr.org/2021/03/05/973624991/9-things-to-know-about-the-unfolding-crisis-in-ethiopias-tigray-region
8. Anderson, J. (2020). *Africa Conflict Series: Ethiopia*. IHS market now a member of S&P. https://ihsmarkit.com/research-analysis/africa-conflict-series-ethiopia.html
9. Deleersnyder, A.-E. (2022). *Ethiopia's Tigray conflict: Exposing the limits of EU and AU early warning mechanisms* (p. 34) [Crisis Group Africa Briefing N°166, Addis Ababa/Dakar/Nairobi/Brussels]. www.kas.de
10. International Crisis Group (ICG). (2021). *Finding a Path to Peace in Ethiopia's Tigray Region—Crisis Group Africa Briefing N°167*. https://reliefweb.int/report/ethiopia/finding-path-peace-ethiopia-s-tigray-region-crisis-group-africa-briefing-n-167-11
11. Gavin, M. (2021). *The Conflict in Ethiopia's Tigray Region: What to Know*. Council on Foreign Relations. https://www.cfr.org/in-brief/conflict-ethiopias-tigray-region-what-know
12. Amnesty International. (2021, November 8). Ethiopia: Sweeping emergency powers and alarming rise in online hate speech as Tigray conflict escalates. *ReliefWeb*. https://reliefweb.int/report/ethiopia/ethiopia-sweeping-emergency-powers-and-alarming-rise-online-hate-speech-tigray
13. Human Rights Watch. (2021, November 8). *Ethiopia: International Action Needed to Prevent Atrocities. Inciting Rhetoric, Sweeping Emergency Regulations Fuel Abuses*. https://www.hrw.org/news/2021/11/08/ethiopia-international-action-needed-prevent-atrocities
14. USAID. (2022). *Ethiopia – Northern Ethiopia Crisis JANUARY 28, 2022* (Fact Sheet #4 Fiscal Year (FY) 2022). https://www.usaid.gov/sites/default/files/documents/2022-01-28_USG_Northern_Ethiopia_Crisis_Fact_Sheet_4.pdf
15. World Vision Ethiopia. (2021). *Rapid Assessment Report on Seven Woredas of East Amhara, North Shewa, North Wollo, and South Wollo Zones* (p. 19) [Rapid Assessment].
16. Amnesty International. (2021). *Ethiopia 2021*. Amnesty International. https://www.amnesty.org/en/location/africa/east-africa-the-horn-and-great-lakes/ethiopia/report-ethiopia/
17. Atlas of Humanity. (n.d.). *Ethiopia, Tigray People*. Atlas Of Humanity. Retrieved 19 August 2022, from https://www.atlasofhumanity.com/tigray
18. Tommasin, D. (2021, April 12). Tigray, Irob and Kunama Ethnic Groups Risk Extinction, Focus on Africa, New and analysis. *Focus on Africa, New and Analysis*. https://www.focusonafrica.info/en/tigray-irob-and-kunama-ethnic-groups-risk-extinction/
19. Wikipedia, the free encyclopedia. (n.d.). *Afar People* (Last edited 05.25.2022). Retrieved 28 May 2022, from https://en.wikipedia.org/wiki/Afar_people
20. Minority Rights Group International. (2018). *World Directory of Minorities and Indigenous Peoples*. https://minorityrights.org/minorities/afar-2/
21. Wilkins, H. (n.d.). *Children Dying in Ethiopia's Afar Region Amid Drought and Conflict, Residents Say*. VOA. Retrieved 19 August 2022, from https://www.voanews.com/a/children-dying-in-ethiopia-s-afar-region-amid-drought-and-conflict-residents-say/6678830.html
22. Ethiopian Statistics Services. (n.d.). *Population and Housing Census 2007 – Affar_Statistical* [Census 2007]. Retrieved 28 May 2022, from https://www.statsethiopia.gov.et/census-2007-2/
23. Anonymous. (2021, November 26). The Curious Case of the Afar People, Unexpected Actors in the Conflict in Northern Ethiopia. *School of Blogal Studies - University of Gothenburg*. https://www.blogalstudies.com/post/the-curious-case-of-the-afar-people-unexpected-actors-in-the-conflict-in-northern-ethiopia
24. Tesfaye, M. G., & Gebrehiwot, M. A. (2020). A "party" at the border: An anthropological take on the Ethio-Eritrean peace deal of 2018. *Cogent Arts & Humanities*, *7*(1), 1727159. https://doi.org/10.1080/23311983.2020.1727159
25. Zewde, B., Yntiso, G., & Berhanu, K. (2014). The Ethiopian diaspora and the Tigray Development Association. In L. Laakso & P. Hautaniemi (Eds.), *Diasporas, Development and Peacemaking in the Horn of Africa*. Bloomsbury Publishing.
26. UNICEF. (2022). *Amhara Regional State 2007/08 – 2015/16* [Budget Brief].
27. Wikipedia, the free encyclopedia. (2022). Amhara Region. In *Wikipedia*. https://en.wikipedia.org/wiki/Amhara_Region
28. EHRC, O. (2021). *EHRC-OHCHR Joint Investigation Report on Tigray Conflict* (p. 156). https://ehrc.org/download/ehrc-ohchr-joint-investigation-report-on-tigray-conflict/
29. AFP, A. (2020, December 30). *Tigray conflict in Ethiopia reawakens land disputes*. https://www.africanews.com/2020/12/30/tigray-conflict-in-ethiopia-reawakens-land-disputes//
30. Wilkins, H. (2022, April 29). Claim of Tigrayan Rebel Withdrawal from Ethiopia's Afar Region Questioned. *VoA*. https://www.voanews.com/a/claim-of-tigrayan-rebel-withdrawal-from-ethiopia-s-afar-region-questioned-/6551044.html
31. Fana Broadcasting. (2022, August). TPLF forcing Tigrayan parents to offer a child in exchange for food: Hermela. *Fana Broadcasting Corporate S.C*. https://www.fanabc.com/english/tplf-forcing-tigrayan-parents-to-offer-a-child-in-exchange-for-food-hermela/
32. Amnesty International, & Human Rights Watch. (2022). *Crimes against Humanity and Ethnic Cleansing in Ethiopia's Western Tigray Zone: Q&A on New Report: 'We Will Erase You from This Land'*. Human Rights Watch. https://www.hrw.org/news/2022/04/06/crimes-against-humanity-and-ethnic-cleansing-ethiopias-western-tigray-zone
33. Amnesty International. (2020, November 12). *Ethiopia: Investigation reveals evidence that scores of civilians were killed in massacre in Tigray state*. Amnesty International. https://www.amnesty.org/en/latest/news/2020/11/ethiopia-investigation-reveals-evidence-that-scores-of-civilians-were-killed-in-massacre-in-tigray-state/
34. Amnesty International. (2022). *Ethiopia: Summary killings, rape and looting by Tigrayan forces in Amhara*. https://www.amnestyusa.org/wp-content/uploads/2022/02/AFR-2552182022-EN_Ethiopia-Summary-killings-rape-and-looting-by-Tigrayan-forces-In-Amhara.pdf
35. Addis Standard. (2022, April 20). News: 65% of people in Irob, NE Tigray facing extreme food insecurity; 87,000 people displaced within eastern zone in March: UN. *Addis Standard*. https://addisstandard.com/news-65-of-people-in-irob-woreda-eastern-tigray-facing-extreme-food-insecurity-87000-people-displaced-within-eastern-zone-in-march-un/

36. Displacement Tracking Matrix (DTM). (n.d.). *Ethiopia—National Displacement Report 11 (December 2021—February 2022)*. Retrieved 2 May 2022, from https://dtm.iom.int/reports/ethiopia-%E2%80%94-national-displacement-report-11-december-2021-%E2%80%94-february-2022
37. NPR. (2020, December 7). *Nearly 50,000 Ethiopians Have Fled to Sudan To Escape War*. https://www.npr.org/2020/12/07/943968767/nearly-50-000-ethiopians-have-fled-to-sudan-to-escape-war
38. ACAPS. (2021). *ACAPS Thematic Report: Ethiopia-Northern Ethiopia crisis: The humanitarian situation one year into the conflict, 03 November 2021* [Thematic Report]. https://reliefweb.int/report/ethiopia/acaps-thematic-report-ethiopia-northern-ethiopia-crisis-humanitarian-situation-one
39. OCHA. (2022). *Ethiopia—Northern Ethiopia Humanitarian Update Situation Report, 3 June 2022* [Situation Report]. https://reliefweb.int/report/ethiopia/ethiopia-northern-ethiopia-humanitarian-update-situation-report-3-june-2022
40. OCHA. (2022). *Northern Ethiopia HUumanitarian update, 27 May 2022* [Situation Report]. https://reports.unocha.org/en/country/ethiopia/card/5EhBh4Xf5z/
41. OCHA. (2022, September). *Ethiopia—Situation Overview—19 Sept 2022*. https://reports.unocha.org/en/country/ethiopia/card/5EhBh4Xf5z/
42. OCHA. (2022). *Northern Ethiopia—Humanitarian update* (p. 20) [Situation Report]. https://reports.unocha.org/en/country/ethiopia/
43. OCHA. (2022). *Ethiopia—Humanitarian Update, 27 Jun 2022* [Situation Report]. https://reliefweb.int/report/ethiopia/ethiopia-humanitarian-update-situation-report-27-jun-2022
44. Wilkins, H. (Director). (n.d.). *Tigrayans Not Allowed to Leave Ethiopian IDP Camps*. Retrieved 3 August 2022, from https://www.voanews.com/a/tigrayans-not-allowed-to-leave-ethiopian-idp-camps/6648972.html
45. Athumani, H. (2022, June). *Ethiopia's Struggling IDPs Face Dilemma: Stay or Return Home?* VOA. https://www.voanews.com/a/ethiopia-struggling-idps-face-dilemma-stay-or-return-home/6630276.html
46. Gebre, T., Hagos, F., Teklu, G., Fisseha, M., & Abera, M. (2020). The Prevalence of Gender-based Violence and Harmful Traditional Practices against Women in the Tigray Region, Ethiopia. *Journal of Asian and African Studies*, *55*(1), 58–75. https://doi.org/10.1177/0021909619867110
47. UNICEF. (n.d.). *Gender-based violence in emergencies*. Retrieved 19 August 2022, from https://www.unicef.org/protection/gender-based-violence-in-emergencies
48. Amnesty International. (2021). *Ethiopia: Troops and militia rape, abduct women and girls in Tigray conflict – new report* [News brief]. https://www.amnesty.org/en/latest/news/2021/08/ethiopia-troops-and-militia-rape-abduct-women-and-girls-in-tigray-conflict-new-report/
49. UNFPA. (2022). *Northern Ethiopia Crisis* (p. 5) [Situation Report].
50. Istratii, R. (2021). *War and domestic violence: A rapid scoping of the literature to understand the relationship and to inform responses in the Tigray humanitarian crisis*.
51. Aucoin, C., Brown, L., Coutu, J., & Gray, R. (2022). *Conflict Diagnostic Ethiopia* (p. 10). Norman Paterson School of International Affairs.
52. Lutheran World Federation. (2020). *Peacebuilding from the grassroots*. https://reliefweb.int/report/ethiopia/peacebuilding-grassroots
53. Kedir, A. (2001). The paradox of Africa's poverty: The role of indigenous knowledge, traditional practices and local institutions—The case of Ethiopia. *Journal of International Development*, *13*, 290–291. https://doi.org/10.1002/jid.738
54. Gesesew, H., Berhane, K., Siraj, E. S., & et al. (2021). The impact of war on the health system of the Tigray region in Ethiopia: An assessment. *BMJ Global Health*, *2021;6:e007328*. https://doi.org/10.1136
55. Mebratie, A. D., Poel, E. V. de, Yilma, Z., & et al. (2014). Healthcare-seeking behaviour in rural Ethiopia: Evidence from clinical vignettes. *BMJ Open*, *4*(2). https://doi.org/10.1136/bmjopen-2013-004020
56. Croke, K. (2020). Original Article: The origins of Ethiopia's primary health care expansion: The politics of state building and health system strengthening; Health Policy and Planning, 35, 2020, 1318–1327. *Oxford University Press in Association with The London School of Hygiene and Tropical Medicine.* https://doi.org/10.1093/heapol/czaa095
57. MSF. (2021, March). Widespread destruction of health facilities in Ethiopia's Tigray region. *Doctors Without Borders*. https://www.doctorswithoutborders.org/latest/widespread-destruction-health-facilities-ethiopias-tigray-region
58. Tesfay, F., & Gesesew, H. (2021, February 24). The health crisis in Ethiopia's war-ravaged Tigray. *Ethiopia Insight*. https://www.ethiopia-insight.com/2021/02/24/the-health-crisis-in-ethiopias-war-ravaged-tigray/
59. OCHA. (2021). *Ethiopia—Northern Ethiopia Humanitarian Update, 23 December 2021* [Situation Report]. https://reliefweb.int/report/ethiopia/ethiopia-northern-ethiopia-humanitarian-update-situation-report-23-dec-2021
60. OCHA. (2022). *Northern Ethiopia Humanitarian Update 24 February 2022* [Situation Report]. https://reliefweb.int/report/ethiopia/ethiopia-northern-ethiopia-humanitarian-update-situation-report-24-february-2022
61. Paltiel, O., & Clarfield, A. M. (2022). Tigray: The challenges of providing care in unimaginable conditions. In *Bmj* (Vol. 376). British Medical Journal Publishing Group.
62. Dadi, A. F. (2022). The mental health consequences of war in northern Ethiopia: Why we should be concerned. *The Lancet Psychiatry*, *9*(3), 194–195. https://doi.org/10.1016/S2215-0366(22)00013-X
63. Assefa, T., Nigussie, N., Mullualem, D., Sinshaw, G., & Adimasu, Y. (2020). The Role of Medicinal Plants in Traditional Medicine in Adwa District, Tigray, Northern Ethiopia. *Asian Plant Research Journal*, 1–11. https://doi.org/10.9734/aprj/2019/v3i3-430067
64. Ethiopian Society of Population Studies. (2008). *Maternal health care seeking behaviour in Ethiopia: Findings from EDHS 2005. Addis Ababa: ESPS, 2008;14–29.* 34.
65. Amref Health Africa. (n.d.). *Health Workers Count – the Story a Community Health Worker in Afar, Amreh Health Africa*. Africa Health Africa. Retrieved 1 June 2022, from https://amref.org/news/health-workers-count-the-story-a-community-health-worker-in-afar-ethiopia/
66. Jones, N., Pincock, K., & Yadete, W. (2021). 'We Are Not Accepted Here': Intersecting vulnerabilities of internally displaced adolescents in Ethiopia. In *Adolescents in Humanitarian Crisis* (pp. 54–77). Routledge.
67. UNICEF. (2022). *Child marriage on the rise in Horn of Africa as drought crisis intensifies*. https://www.unicef.org/press-releases/child-marriage-rise-horn-africa-drought-crisis-intensifies
68. Grandjean, M. (2022, May 2). Girlhood Annihilated: Rates of Child Marriage Are Soaring in Ethiopia. *Impakter*. https://impakter.com/girlhood-annihilated-child-marriage-in-ethiopia/
69. Favara, M., Hittmeyer, A., Porter, C., Singhal, S., & Woldehanna, T. (2022). Young people, mental health, and civil conflict: Preliminary findings from Ethiopia's Tigray region. *Psychiatry Research Communications*, *2*(1), 100025. https://doi.org/10.1016/j.psycom.2022.100025

70. USAID. (2022). *Ethiopia – Northern Ethiopia Crisis, APRIL 26, 2022* [Fact Sheet #6, Fiscal Year (FY) 2022]. https://www.usaid.gov/sites/default/files/documents/2022-04-26_USG_Northern_Ethiopia_Crisis_Fact_Sheet_6.pdf
71. Negash, E., Nyssen, J., & Annys, S. (2021). *How Ethiopia's conflict has affected farming in Tigray*. The Conversation. http://theconversation.com/how-ethiopias-conflict-has-affected-farming-in-tigray-166229
72. WFP. (2022, March). *Tigray: Emergency Food Security Assessment*. https://www.wfp.org/publications/tigray-emergency-food-security-assessment
73. UNICEF. (2022). *Ethiopia WASH Cluster Humanitarian Dashboard (As of March 2022)* [WASH Cluster].
74. OCHA. (2022). *Northern Ethiopia- Humanitarian update Last updated: 29 April 2022* [Situation Report].
75. UNICEF Ethiopia. (2021). *Emergency WASH Rapid Response Mechanism in Ethiopia* [RRM update]. UNICEF. https://www.unicef.org/ethiopia/reports/emergency-wash-rapid-response-mechanism
76. OCHA. (2022). *Northern Ethiopia-Humanitarian update Last updated: 20 May 2022* [Situation Report]. https://reports.unocha.org/en/country/ethiopia
77. Als, D., Meteke, S., Stefopulos, M., & et al. (2020). Delivering water, sanitation and hygiene interventions to women and children in conflict settings: A systematic review. *BMJ Global Health*. https://doi.org/10.1136/ bmjgh-2019-002064
78. ICRC. (2019, April 16). *ICRC helps 12,000 displaced people in North Ethiopia access water, sanitation services*. https://www.icrc.org/en/document/icrc-helps-12000-displaced-persons-north-ethiopia-access-water-sanitation-services
79. People in Need. (2022, May 13). *Having access to water is a matter of survival in conflict-affected areas in the Tigray region of Ethiopia*. People in Need. ttps://reliefweb.int/report/ethiopia/having-access-water-matter-survival-conflict-affected-areas-tigray-region-ethiopia
80. Oxfam. (2022, June 16). *Looming rainy season in Northern Ethiopia to bring more risks of disease and hunger, as aid still falls short*. Oxfam International. https://www.oxfam.org/en/press-releases/looming-rainy-season-northern-ethiopia-bring-more-risks-disease-and-hunger-aid-still
81. MeryCorps. (2015). *Building Community Resilience During Violent Conflict: Lessons Learned from Mercy Corps' Stabilizing Vulnerable Communities Program in the Central African Republic (CAR*. https://europe.mercycorps.org/sites/default/files/2019-11/Building%20Resilience%20During%20Conflict%20-%20Policy%20One-Pager_0.pdf
82. Menbere, G., & Skjerdal, T. (2008). The potential of dagu communication in north-eastern Ethiopia. *Media Development*, *55*, 19–21.
83. Nigussie, H. (2016). Indigenous Communication Forms and Their Potential to Convey Food Security Messages in Rural Ethiopia. *Indian Journal of Human Development*, *10*(3), 414–427. https://doi.org/10.1177/0973703017698895
84. Federal Democratic Republic of Ethiopia. (2022). *Response – Recovery – Resilience for Conflict-affected communities in Ethiopia: Stakeholder Engagement Plan (3R-4-CACE) (P177233)*. https://www.mofed.gov.et/media/filer_public/77/a9/77a9215a-0a0f-40ac-8a5e-1bfb95da2c08/3r4cac_draft_sep-_p151777_-_mof_comments_11march22docx_clean_version.pdf

# ምስጋና

ይህ አጭር መግለጫ ወይም ጽሁፍ በኢንስቲትዩትኦፍ ዴቨሎፕመንት ስተዲስ (IDS) ከታቢታ ሕሪኒክ ድጋፍ ጋር ሄራን አበበ እና ጌታቸው በላይነህ የጻፉት ነው። በተጨማሪም ከኢዛና አምደወርቅ (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) ፣ ቀለመወርቅ ታፈረ (መቀሌ ዩኒቨርሲቲ) እና ዮሚፍ ወርቁ (ገለልተኛ የሰብዓዊ ጉዳዮች አማካሪ) ለተደረገዉ የባለሙያዎች አስተያየትም ምስጋና ልንሰጥ እንወዳለን። ተጨማሪ ግምገማዎች በሃይሊ ማክግሪጎር (IDS) እና ሌስሊ ጆንስ (Anthrologica) ተሰጥተዋል።

# የግንኙነት አድራሻ

አጭር መግለጫውን ፣ መሳሪያዎችን ፣ ተጨማሪ ቴክኒካዊ እውቀትን ወይም የርቀት ትንታኔን በተመለከተ ቀጥተኛ ጥያቄ ካለዎት፣ ወይም በአማካሪዎች አውታረመረብ መግባት ከፈለጉ፣ እባክዎን በአኒ ሎውደን (a.lowden@ids.ac.uk) ወይም ኦሊቪያ ቱሎክ (oliviatulloch@anthrologica.com) በኢሜል በመላክ የማህበራዊ ሳይንስ በሰብአዊ ድርጊት መድረክን ያነጋግሩ።

የማህበራዊ ሳይንስ በሰብአዊ ድርጊት(SSHA)፣ በልማት ጥናት ኢንስቲትዩት(IDS) ፣ አንትሮሎጂካ(Anthrologica) እና በለንደን የንፅህና እና የትሮፒካል ሕክምና ትምህርት ቤት(LSHTM) መካከል ያለ ጥምረት ነው። ይህ ሥራ በእንግሊዝ የውጭ፣ የጋራ ሀብት እና ልማት ቢሮ (UK Foreign, Commonwealth and Development Office )እና የዌልኮም ግራንት ቁጥር (Wellcome Grant Number ) 225449/Z/22/Z ተደግፏል። የተገለጹት ሃሳቦች የጸሐፊዎቹ ሲሆኑ የገንዘብ ሰጪዎችን፣ ወይም የIDS፣ Anthrologica ወይም LSHTM አስተያየቶችን ወይም ፖሊሲዎችን አያንጸባርቁም።

# እንቀራረብ

@SSHAP_Action info@socialscience.org www.socialscienceinaction.org SSHAP newsletter

**ምንጭ ለመጥቀስ:** Abebe, H. and Belaineh, G., (2022) 'Key Considerations: Social Science Perspectives for Emergency Response to the Conflict in Northern Ethiopia,' Brighton: Social Science in Humanitarian Action (SSHAP). DOI: DOI: 10.19088/SSHAP.2022.042

እ.ኤ.አ ጥቅምት 2022 ታተመ

© Institute of Development Studies 2022

ይህ በCreative Commons Attribution 4.0 International License (CC BY) ውሎች ስር የሚሰራጭ ክፍት መዳረሻ ወረቀት ሲሆን፣ ዋና ጸሃፊዎቹ እና ምንጮቹ ዕዉቅና ካገኙ እና ማሻሻያዎች እስከተጠቀሱ ድረስ በማንኛውም ሚዲያ ውስጥ ያልተገደበ አጠቃቀም፣ ስርጭት እና መራባትን ይፈቅዳል። http://creativecommons.org/licenses/by/4.0/legalcode